# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 358 ነሐሴ 28 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







## በመዲናዋ በ6 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር የተገነቡት የገበያ ማዕከላት በቅርቡ ወደ ሥራ ይገባሉ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡-በመዲናዋ በስድስት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር የተገነቡት የግብርና ምርቶች ማከማቻና መሸጫ ማዕከላት በቅርቡ ወደ ሥራ እንደሚገቡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሜጋ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሜጋ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት ኮንትራት አስተዳደር ዳይሬክተር አቶ ዳዊት ጥበቡ እንደገለጹት፤ ከተማ አስተዳደሩ የህብረተሰቡን ችግሮች ለመቅረፍ በስድስት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር ሦስት የግብርና ምርቶች መሸጫ ገበያ ማዕከላት እየተገነቡ ይገኛሉ።

እንደ አቶ ዳዊት ገለጻ፤የግብርና ምርቶች ማከማቻና መሸጫ ማዕከሉ በአያት ፣በኮልፌና ሰሚት የሚገነቡ ሲሆን ሁሉም በመጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ።

የገበያ ማዕከላቱ የተገነቡት በዘጠኝ ወራት መሆኑን የጠቀሱት አቶ ዳዊት፤ የግንባታ አፈጻጸማቸው 94 በመቶ ላይ ይገኛል ብለዋል።

ከተማ አስተዳደሩ የህብረተሰቡን ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችሉ ዘርፈ ብዙ ፕሮጀክቶችን እያስገነባ መሆኑን ጠቅሰው በገበያ ማዕከላቱ አትክልት፣ ጥራጥሬና የግብርና ምርቶች ለህብረተሰቡ እንደሚቀርቡ ተናግረዋል።

የማዕከላቱ ዓላማ ሸማቹንና አምራቹን ማገናኘት መሆኑን የገለጹት አቶ ዳዊት፤ በግብይት ሥርዓቱ ውስጥ ደላሎች ሳይገቡ ምርቶችን በቀጥታ ለተጠቃሚው ለማድረስ የሚያስችሉ መሆኑን ገልጸዋል።

ማዕከላቱ መጋዘኖች፣ የጅምላና ችርቻሮ መሸጫዎች

ፎቶ - አዮብ ተፈሪ




በለሚ ኩራ ክ/ከተማ እየተገነባ ያለው የግብርና ምርቶች ማከማቻና መሸጫ ማዕከል

የሚገኙባቸው መሆናቸውን ጠቅሰው በተለይም የግብይት ሥርዓቱ በቴክኖሎጂ በመታገዝ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ነው ብለዋል።

የሜጋ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽህፈት ቤት የግብርና ምርቶች መሸጫ ገበያ ማዕከላት ፕሮጀክቶች አስተባባሪ መሀንዲስ ጉርሜሳ ረታ በበኩላቸው፤የግብርና ምርቶች መሸጫ ገበያ ማዕከላት


በመዲናዋ በ6 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል












## የባንኮችን የክፍያ ሥርዓት በማዘመን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ ይጠበቃል

### -ንግድ ባንክ የዲጅታል አገልግሎት ብቻ የሚሰጥበትን ዐቢይ ቅርንጫፍ አስመርቋል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ ፡- በሀገሪቱ የሚገኙ ባንኮችን የክፍያ ሥርዓት በማዘመን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ እንደሚጠበቅ የገንዘብ ሚኒስቴር ገለጸ። የኢትዮጵያ


የባንኮችን የክፍያ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል


## ለመጪው በዓል ከተገዛው የምግብ ዘይት 2 ነጥብ 4 ሚሊዮን ሊትሩ ወደ ሀገር ገብቷል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ለመጪው የዘመን መለወጫ በዓል ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ሊትር የምግብ ዘይት ወደ ሀገር ውስጥ ማጓጓዙን የኢትዮ - ጅቡቲ ምድር ባቡር አክሲዮን ማህበር አስታወቀ። ተጨማሪ ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ሊትር ዘይት ጅቡቲ ላይ ወደ ባቡር እየተጫነ መሆኑም ተነግሯል።

በኢትዮ - ጅቡቲ ምድር ባቡር አክሲዮን ማህበር የኮርፖሬት ስትራቴጂ ቢሮ ኃላፊ አቶ አሚኑ ጁሀር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የኢትዮ - ጅቡቲ ምድር ባቡር የዕቃዎች እና የመርከቦች የባህር ላይ የቆይታ ጊዜ እንዲሻሻል፣ የዲሜሬጅ ክፍያ እንዲቀንስ እና ምርቶችን በፍጥነት ወደ ተጠቃሚው እንዲደርሱ የበኩሉን ሚና እየተወጣ ይገኛል።

በ2015 በጀት ዓመት ከሁለት ሚሊዮን ቶን በላይ እቃዎችን በማጓጓዝ ከሀገሪቱ አጠቃላይ የገቢና ወጪ ጭነት የ15 በመቶ ድርሻ መሸፈን ችሏል ያሉት አቶ አሚኑ፤ የኢትዮ - ጅቡቲ ምድር ባቡር ሃያ ሚሊዮን ሊትር የምግብ ዘይት ከጅቡቲ ወደ ሀገር ውስጥ እያጓጓዘ ነው። የአዲስ ዓመት በዓልን ምክንያት በማድረግ ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ሊትር የምግብ ዘይት ወደ ሀገር ውስጥ መጓጓዙን ነው የተናገሩት።



አቶ አሚኑ ጁሀር

ተጨማሪ ሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን ሊትር ዘይት ጅቡቲ ላይ ወደ ባቡር እየተጫነ መሆኑን የገለጹት አቶ አሚኑ፤ በበዓላት ወቅት የምግብ ዘይት ፍጆታ በከፍተኛ ሁኔታ የሚጨምር በመሆኑ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት እና የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን የምግብ ዘይትን በድጎማ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባሉ ብለዋል።


ለመጪው በዓል ከተገዛው... ወደ ገጽ 5 ዞሯል







## በኢትዮጵያ የመደጋገፍና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ መስፋፋትና ዘላቂ መሆን ይኖርበታል

### - ሚኒስቴሩ ከዘጠኝ ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ 13 የአቅመ ደካሞች ቤቶችን ገንብቶ አስረከበ


ገጽ 5










# በጳጉሜን ቀናቶች፡-
## -ሰው ተኮር ተግባራት ይከናወናሉ
## - ለአንጋፋ ባለሙያዎች እውቅና ይሰጣል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በመጪው የጳጉሜን ስድስት ቀናቶች የከተማዋን ነዋሪዎች የሚያሳትፉ ሰው ተኮር ተግባራት እንደሚከናወኑና ለአንጋፋ ባለሙያዎች እውቅና እንደሚሰጥ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮሙኒኬሽን ቢሮ ገለጸ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮሙኒኬሽን ቢሮ የጷጉሜ ስድስት ቀናቶች አጠቃላይ ተግባራትና የከተማ አቀፍ መርሀ ግብሮችን አስመልክቶ ትናንት መግለጫ ሰጥቷል።

በመግለጫው የአስተዳደሩ የኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ እናትአለም መለሰ እንዳስታወቁት ፤ በከተማዋ በጳጉሜን ቀናቶች የተለያዩ ሰው ተኮር ሥራዎች በስፋት የሚሰሩ ይሆናል። በጳጉሜን 1 የአገልጋይነት ቀን ሲሆን በከተማዋ ከጠዋቱ 12 ሰአት ጀምሮ ነፃ ትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል። ለአንጋፋ መምህራን እና ለጤና ባለሙያዎች ምስጋና እውቅና የሚሰጣቸው ይሆናል።

ጳጉሜን 2 የመስዋዕትነት ቀንን በማስመልከት በሁለም ተቋማት እና ወረዳዎች ሰንደቅ ዓላማ የመስቀል ሥነ-ሥርዓት የሚከናወን መሆኑን አመልክተው፤ በዚህም ለሠራዊቱ እና የፀጥታ አካላት ክብር ይሰጣል፣ የፓናል ውይይቶች ይደረጋሉ። በሁሉም ክፍለ ከተሞች እና ተቋማት የደም ልገሳ መርሃ- ግብር እንደሚከናወን ገልጸዋል።

ሌላው ጳጉሜን 3 የበጎነት ቀን አስመልክቶ በእለቱ በተለያዩ ቦታዎች የተገነቡ 860 ቤቶች ለአቅመ ደካሞች የሚተላለፉ መሆኑን ገልጸው፤ በማዕከል ደረጃ ፤ ሁሉም ክፍለ ከተሞች እና ተቋማት ማዕድ ማጋራት መርሃ-ግብር ይከናወናል። በተጨማሪም በጉለሌ ክፍለ ከተማ ቀጨኔ አካባቢ 20ኛ የሆነው የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል የሚመረቅ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የአምራችነት ቀን የሚል ስያሜ በተሰጠው በጳጉሜን 4 ደግሞ በሁሉም ክፍለ ከተሞች የሀገር ውስጥ ምርቶች በተለያዩ የገበያ ባዛርና ኤግዚቢሽን ይከፈታሉ። የአያት የገበያ ማዕከል ምርቃት እንደሚከናወን ተናግረዋል።

በጳጉሜን 5 የትውልድ ቀን በ11ዱም ክፍለ ከተሞች የመምህራን እና የወላጆች የውይይት መድረኮች እና የማስ ስፖርት እንቅስቃሴ በማድረግ የሚታወስ ሲሆን በማዘጋጃ ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወላጅ ያጡ ሕጻናትን አሳዳጊዎች ርክክብ የማድረግ ሥርዓት የሚከናወን መሆኑን አስታውቀዋል።

ጳጉሜን 6 የአብሮነት ቀንን በሁሉም ክፍለ ከተማ እና ወረዳዎች ነዋሪዎች ስለ አብሮነትን የሚወያዩባቸው መድረኮች የሚካሄድ መሆኑን ጠቁመው፤ የዋዜማ የመዝናኛ ሙዚቃ ኮንስርቶች እንደሚኖሩም ገልጸዋል።

# በሀገሪቱ ለሚከሰቱ የትራፊክ አደጋዎች 70 በመቶ የሚሆነው ከአሽከርካሪዎች ጋር የተያያዘ ነው

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ ለሚከሰቱ የትራፊክ አደጋዎች 70 በመቶ የሚሆነው መንስኤ ከአሽከርካሪዎች ጥፋት ጋር የሚያያዝ መሆኑን የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር ገለጸ።

ለመንገድ ደህንነት መረጋገጥ የተሻለ አስተዋጽኦ ላበረከቱ አካላት ሀገር አቀፍ የእውቅናና የምስጋና መርሃ ግብር ትናንት ተካሂዷል።

የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስትር ዶክተር አለሙ ስሜ በሥነ ሥርዓቱ ላይ እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ ለሚከሰተው የትራፊክ አደጋ 70 በመቶ የሚሆነው መንስኤ ከአሽከርካሪዎች ጋር የተያያዘ ነው።

የትራፊክ አደጋ ዓለም ላይ ለሞት መንስኤ ከሚሆኑ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች አንዱ መሆኑን ገልጸው፤ የሰው ሕይወት እያጠፉ ካሉ ተላላፊ እና ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች በስምንተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ከተሽከርካሪዎች ጋር ተያይዞ ለሚከሰተው አደጋ በርካታ መንስኤዎች መኖራቸውን የተናገሩት ሚኒስትሩ፤ በቂ የማሽከርከር ብቃት ሳይኖራቸው በአቋራጭ መንጃ ፈቃድ የሚያገኙ አሽከርካሪዎችን እና በሥነ ምግባር ጉድለት አደጋ እንዲከሰት መንስኤ የሚሆኑ አሽከርካሪዎች መኖራቸውን ጠቅሰዋል።

በተጨማሪም የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ችግር፤ የመንገዶች ምቹ አለመሆንና መንጃ ፈቃድ የሚሰጡ አካላት የተሰጣቸውን ኃላፊነት በብቃት አለመወጣት ለአደጋው መንስኤ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

ሚኒስትሩ እንደተናገሩት፤ በሀገሪቱ የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው። በዚህም፤ የትራፊክ አደጋውን ከመቀነስ አንጻር ለውጦች እየታዩ ነው።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በትራፊክ አደጋ የሚጠፋውን የሰዎች ሕይወት ለመታደግ እና የሚወድመውን ንብረት ለማስቀረት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን አውስተው፤በ2016 ዓ.ም የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ ሕግና ደንብን ከማስጠበቅ አንጻር ትኩረት ተሰጥቶ የሚሠራ ይሆናል ሲሉ ገልጸዋል።

የመንገድ ደህንነትና መድን ፈንድ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ጀማል አባሶ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ 2015 ዓ.ም የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ ኢትዮጵያ ጠንካራ አቋም ይዛ በመሥራቷ ትልቅ ለውጥ ሊመዘገብ ችሏል።



ዶክተር አለሙ ስሜ



አቶ ጀማል አባሶ

በዚህም በበጀት ዓመቱ የሞቱ ሰዎች ቁጥር ከ2014 ዓ.ም ጋር ሲነፃፀር በ394 ሰዎች እንደቀነሰ ተናግረዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለፃ ፤በ2010 ዓ.ም 936 ሺህ መኪና በሀገሪቱ ሲኖር የሞቱ ሰዎች ቁጥር ከአምስት ሺህ በላይ ነው፤ በአሁኑ ጊዜ በሀገሪቱ አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን መኪና ቢኖርም በመኪና አደጋ የሞቱ ሰዎች ቁጥር 3 ሺህ 577 ነው።

ከንብረት አንጻር በትራፊክ አደጋ የሚወድመው ንብረት መቀነሱን አመልክተው፤ የዝግጅቱ ዓላማ ይህ ለውጥ እንዲመጣ ሚናቸውን በብቃት ለተወጡ አካላት ምስጋና በመስጠት በቀጣይ የትራፊክ አደጋን የበለጠ ለመቀነስ ዓላማ ያደረገ መሆኑን አቶ ጀማል ተናግረዋል።

# ለክልሉ ሰላምና ደህንነት መረጋገጥ ቅድሚያ የሚሰጡ አመራሮችን ወደፊት ለማምጣት በትኩረት እንሰራለን
## -የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ ለሰላምና ደህንነት መረጋገጥ ቅድሚያ የሚሰጡ አመራሮችን በየደረጃው ወደ ፊት ለማምጣት በትኩረት እንሠራለን ሲል የአማራ ክልላዊ መንግሥት አስታወቀ።

የአማራ ክልል የጸጥታ ምክር ቤት የክልሉን ወቅታዊ ሁኔታ የሚገመግምና የቀጣይ አቅጣጫዎች ላይ ያተኮረ ውይይት በባህር ዳር ከተማ ተካሂዷል።

የክልሉ መንግሥት የጸጥታ ተቋማትን ለማጠናከር የሰላምና ጸጥታ፣ ፖሊስ ኮሚሽን፣ የሚሊሻና ማረሚያ ቤቶች ሃላፊዎችንና ምክትል ሃላፊዎችን ትናንት መሾሙ ይታወሳል።



ውይይቱን አስመልክተው የክልሉ የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ዶክተር መንገሻ ፈንታው እንደገለጹት፤ አዲስ የተዋቀረውን የጸጥታው ዘርፍ ተቋማት እርስ በእርስና ከጸጥታ ምክር ቤቱ አባላት ጋር የመተዋወቅ፣ ወቅታዊ ሁኔታዎችን የመገምገምና ቀጣይ አቅጣጫዎች ላይ ዛሬ ውይይት ተካሂዷል።

በክልሉ ያጋጠመውን የጸጥታ ችግር በመፍታት የሕዝቡ ዘላቂ ሰላምና ደህንነት በሚረጋገጥበት ሁኔታ ላይ መምከሩንም አመልክተዋል።

በተጨማሪም የክልሉን ሰላም ወደ ነበረበት ለመመለስ ያለውን ቁርጠኝነት፣ የቀጣይ እቅድና የሚያስፈልጉ ድጋፎችን በመለየት በጋራ ለውጥ ለማምጣት ያለመ ጭምር መሆኑንም አስረድተዋል።

በአዲስ መልክ መልሶ በተዋቀሩት የጸጥታ ተቋማትም እስከ ወረዳና ቀበሌ ያለውን መዋቅራቸውን እንደገና በማደራጀት በሰላምና ደህንነት ላይ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት እንሠራለን በማለት ወደ ሥራ መገባቱንም ተናግረዋል።

በምክክር መድረኩ ላይ በተለይም ለክልሉ ሰላምና ደህንነት መረጋገጥ ቅድሚያ የሚሰጡ አመራሮችን በየደረጃው ወደ ፊት ለማምጣት በትኩረት እንሠራለን መባሉንም ዶክተር መንገሻ አስታውቀዋል።

የክልሉ የጸጥታ ምክር ቤት የአማራ ክልልን ወደ ነበረበት ሰላም ለመመለስ ከመከላከያ ሠራዊት ጋር በትብብር በመሥራት አሁን የሚታየውን የሰላም መሻሻል ማስቀጠል እንደሚገባ ተመላክቷል።

እንደ ኢዜአ ዘገባ የክልሉ የጸጥታ ተቋማት በቀጣይ ለሚያከናውኑት የሰላምና ደህንነት መረጋገጥ ተግባራት የመስተዳድር ምክር ቤቱ መደገፍ የሚገባውን ለይቶ በማቅረብ መዋቅሩ ፈጥኖ ወደ ሥራ እንዲገባ እንደሚደረግም ተገልጿል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አዲሱ ዓመት የተስፋችን መስሪያና ማብሰሪያ እንዲሆን!

አዲስ ዓመት ከዓመቱ አዲስነት በላይ ይዞት ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀው አዲስ ነገር በብዙዎች ዘንድ ትልቅ ትኩረት ይሰጠዋል። ከዚህ የተነሳም አንዳንዶች የሕይወታቸው መታጠፊያ መንገድ አድርገው በመውሰድ እራሳቸውን በሁለንተናዊ መልኩ የሚያዘጋጁበት ሁኔታ ይስተዋላል። በዚህም ስኬታማ መሆን የቻሉ ጥቂት አይደሉም።

ይህ ትናንቶቻችን ከራስ የመሆን መፈለግ ጋር በአግባቡ ከመገምገም የሚነሳው የነዚህ ሰዎች የአዲስ ዓመት አቀባበል ፤ አዲሱን ዓመት በተቻለው ሁሉ መሆን ለሚፈልጉት መሻታቸው ስኬት የሚሆንበትን አቅም በመፍጠር እና አሱን በአግባቡ ከራሳቸው ጋር በማስተሳሰር ተስፋቸውን የሚያድሱበት ነው።

ይህ በአዲስ ዓመት ዋዜማ ላይ የሚከናወን እራስን በተስፋ ውስጥ የማደስ ፤ ለዚህ የሚሆን መንፈሳዊ ፣ አእምሯዊና አካላዊ ዝግጁነት መፍጠር ከቀደሙት ትውልዶች ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ፤ ወደፊትም ቀጣይ የሆነ ትልቅ ሰብዓዊ እሴት እንደሆነም ይታመናል።

እንደ ማህበረሰብም ፤ አንድ ማህበረሰብ በተመሳሳይ መልኩ ፤ በአዲስ ዓመት ዋዜማ ላይ አዲሱን ዓመት በተስፋ መቀበል የሚያስችል መንፈሳዊ ፣ አእምዊና አካላዊ ዝግጁነት የሚያላብሱ ተግባራትን ይከውናል። ለዚህ የሚሆኑም መንፈሳዊ ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ እሴቶች ይኖሩታል።

እነዚህ እሴቶች ትናንቶችን ከማህበረሰቡ የመሆን መሻት አንጻር በተጨባጭ የሚገመግሙ ፤ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ለይተው ፤ ጠንካሮቹ የሚጎለብቱበትን ፤ ደካሞቹ የሚስተካከሉበትን የሚጠቁሙ ናቸው። ከዚህ ባለፈ ነውሮችን ፣ ከነውሮች በስተጀርባ ያሉ የአመለካከት መዛነፎች የሚያወግዙ ናቸው።

ይህ እውነታ እንደሀገር በእኛም ማህበረሰብ (ህዝብ) ውስጥ ዘመናት ያስቆጠረ፣ ዛሬም በስፋት የሚስተዋል ነው። አዲሱ ዓመት በአደይ አበባ ተሞሽሮ ሲመጣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ለትናንት መሻቱ አዲስ ተስፋ ሰንቆ ለመንቀሳቀስ ከራሱ ጋር የሚመክርበት ፣ በምክሩም ራሱን አሳምኖ የሚቆምበት ነው።

ለዚህም በመንፈሳዊ ፣ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶቹ ውስጥ ያሉ ተስፋ አቆጥቋጭ እሴቶች ያላቸው ሚና ከፍ ያለ ነው። እነዚህ አሴቶች ከትናንት ስህተት ተምሮ መቆም ፣ መራመድ ፣ ከራስ ጋር በሚደረግ እርቅ (በአዲስ የማንነት ግንባታ) ነገዎችን የተስፋ መስሪያና ማረፊያ ማድረግ እንደሚቻል አበክረው የሚመክሩ ናቸው።

ይህ አዲስ ዓመት በራሱ የሚጭረው አዲስ የማንነት ግንባታ መነቃቃት ከግለሰብ አልፎ እንደሀገር ለጀመርነው ድህነትን አሸንፎ የመሻገር አዲስ የታሪክ ጉዞ ዋነኛ አቅም ሊሆን እንደሚችልም ይታመናል።

በተለይም በዚህ የአዲስ ዓመት ዋዜማ ትናንቶቻችንን በአግባቡ እና በታማኝነት መገምገም ከቻልን ፣ አዲሱ ዓመት ይዟቸው የሚመጣቸው ነገዎች የተስፋዎቻችን መሥሪያና ማብሰሪያዎች መሆን ስለመቻላቸው ብዙም የሚያከራክር አይሆንም።

ይህን በተጨባጭ እውን ለማድረግ ፤ በነዚህ ቀናቶች ውስጥ በጥድፊያ ከተሞላው የጥፋት መንገዶቻችን ቆም ብለን ስለተስፋችን እየተጓዝንበት ስላለው መንገድ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ምንነት በአግባቡ መገምገም ይጠበቅብናል።

በመንገዳችን ላይ አሜኬላ የሆኑብን ነውሮቻችን ምን ያህል ያልተገባ ዋጋ እያስከፈሉን ስለመሆኑ በሰከነ መንፈስ ልንመረምራቸው ፣ ነውርነታቸው እስከምን ድረስ መንፈሳዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ አሴቶቻችንን እየተፈታተኑት እንደሆነም ልናጤነው ይገባል።

በተለይም ስለ ሕዝብ እና ስለ ሀገር ፣ ድህነትና ኋላቀርነትን አሸንፎ የበለጸገች ሀገር ስለመመስረት እያዜምን ፣ በተጨባጭ እየተጓዝን ስላለው የጥፋት መንገድና መንገዱ እንደግለሰብ ሆነ እንደሀገር እያስከፈለን ስላለው ያልተገባ ዋጋ በሃላፊነት መንፈስ ልናስብ ይገባል።

የዛሬው በግጭትና በሁከት የተሟሟቀው የታሪክ ጉዟችን ከኛም አልፎ ለመጭዎች ትውልዶች ጥሎት ሊሄድ ስለሚችለው ጠባሳ ፤ ጠባሳው በመጭዎቹ ትውልዶች ዘላቂ ሰላም ላይ ሊፈጥር ስለሚችለው አሉታዊ ተጽእኖ ፤ ልጅ ወልዶ ለልጆቹ ነገዎች በብዙ እንደሚቃትት ወላጅ አስበን ልንቀሳቀስ ይገባል። በዚህም አዲሱ ዓመት ከአዲስ ቀናቶች ስብስብነቱ ባለፈ የተስፋችን መስሪያና ማብሰሪያ ማድረግ እንችላለን።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ:- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዲፕሎማሲያዊ ባህሉቻችንን አሻሽለን ከብሪክስ ብሄራዊ ጥቅሞቻችንን እናስጠብቅ

አሸብር ኃይሉ

በዓለም ታሪክ ኢትዮጵያ ከየትኛውም ሀገር ቀድማ ያልጀመረችው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁነቶች የሉም ቢባል ማጋነን አይደለም። በርካታ ሥልጣኔዎችን ከየተኛውም ዓለም በፊት እንደጀመረች እና እነኚህን ሥልጣኔዎቿን ለዓለም ሕዝብ ያበረከተች ስለመሆኗ በተለያዩ መጽሐፍት እና ጥናታዊ ጽሁፎች ተመላክቷል።

ነግር ግን በቀደመው ጊዜ ከዓለም ሀገራት ቀዳሚ መሆን እና ለዓለም ሕዝብም የተለያዩ ሥልጣኔዎችን አበርክተን ነበር ማለት በአሁኑ ጊዜ በሥልጣኔ ማማ ላይ ነን ማለት አይደለም። በቀደሙት ዘመናት ከፊት መሆን በዚህ ወቅት ለሚኖረው የዓለም የሥልጣኔ አርሾ ሊሆን ይችላል እንጂ አሁን ላይ ላለን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚ አቅም ሊሆን አይችልም ።

አሁን ላይ ቀዳሚ መሆን ከተፈለገ በቀደመው ጊዜ ጠንካራ እንድንሆን ያስቻሉ ሀገር በቀል እውቀቶች እና አሰራሮች መመርመር ፤ ዛሬን መዋጀት በሚችሉበት አቅም ተግባራዊ ማድረግ ፣ለዚህ የሚሆን አዲስ ሀገር አሻጋሪ ትርክት መፍጠር ያስፈልጋል።

ዓለም ሁልጊዜም በተቃርኖ ውስጥ ናት። ተቃርኖዎች በራሳቸው አሉታዊ እና አወንታዊ ተጽዕኖ ማሳደራቸው የማይቀር ነው። እነኚህ ተቃርኖዎች ሜታፊዚክሳዊ ወይም ዳያሌክታዊ ምክንያት እና ውጤት ይኖራቸዋል። እነኚህን ተቃርኖዎች በቅጡ በመረዳት አወንታዊ ውጤት እንዲኖራቸው በማድረግ ለሥልጣኔ አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል።

አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱ የዓለም አቀፍ ግንኙነት ነው ። ከዓለም አቀፍ ግንኙነቶች ተጠቃሚ መሆን የሚቻለው ግንኙነታችንን ተገማች እና ኢተጋማች በሆነ መልኩ ማደራጀት እና ማዘመን ስንችል ነው።

በዘመናዊ ዓለም ኢትዮጵያ በበርካታ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ ከአፍሪካ ብሎም ከዓለም ሀገራት ግንባር ቀደም ሆና አይተናታል። ነገር ግን ለዓለም ፖለቲካል ኢኮኖሚ ከምታበረክተው አብርክቶ አንጻር ምን ያህል ተጠቃሚ ናት? የሚለውን መገምገም ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ በዓለም ፖለቲካል ኢኮኖሚ ካላት ተሳትፎ አንጻር ተጠቃሚ አይደለችም። ለዚህም በርካታ ማሳያዎችን ማቅረብ ይቻላል። አንደኛ ኢትዮጵያ የዓለም ማህበር ( League of Nation) ሲመሠረት መስራች ሀገር ባትሆንም ከአፍሪካ ብቸኛዋ ከቅኝ ግዛት ነጻ አባል ሀገር ነበረች።

በአባልነት ጊዜዋም ለማህበሩ ሁለንተናዊ እድገት በርካታ ሥራዎችን ሰርታለች። ይሁን እንጂ ሌላኛዋ የዓለም ማህበር አባል ሀገር የነበረችው ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረራ ለመያዝ ስትመጣ አንድም ሀገር ለኢትዮጵያ አለሁልሽ ያላት አልነበረም።

ይባስ ብለው ጣሊያን በሶማሊያ ወልወል በኩል ወረራዋን ስታስፋፋ ኢትዮጵያ ያደረገችው መከላከል እንደ ወንጀል ተቆጥሮ “በድሎ ካሱኝ ፤ እሾህ ይዞ እጄን ዳብሱኝ” እንዲሉ በግፍ የወረረችን ጣሊያን በወልወል በኩል ኢትዮጵያ ጥቃት ስለፈጸመችብኝ ካሳ ትክፈለኝ አለች። አብዛኛው የዓለም ማህበር አባል ሀገራትም «ለጣሊያን ካሳ ያስፈልጋታል» ሲሉ ፍትህን አርቀው ቆፍረው ቀበሯት። ኢትዮጵያም ብዙ በደከምችበት ማህበር ክህደት ተፈጽሞባታል።

ሁለተኛ ኢትዮጵያ በመስራችነት ከምትታወቅባቸው ማህበራት አንዱ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (United Nation) በዋነኝነት ይጠቀሳል። ኢትዮጵያ ድርጅቱን ከመመስርትም አልፋ አንድ ሉዓላዊ ሀገር በሌላ ሉዓላዊ ሀገር ብትወረር ማህበሩ መውሰድ የሚገባቸው ርምጃዎች ምን መምሰል አለባቸው የሚለውን ሕግ እንደ አንድ የማህበሩ ሕግ እንዲሆን አድርጋለች ። ከዚህ አኳያ ልጅ አክሊሉ ኃብተወልድ የፈጸሙት ገድል ሁሌም በታሪክ ሲዘከር የሚኖር ነው።

ከዚህ ባሻገር ኢትዮትጵያ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የተደረገላትን ጥሪ ተቀብላ በዓለማችን ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ በበርካታ ሀገራት በሰላም አስከባሪነት ተሳትፋለች፤ አሁንም እየተሳተፈች ነው። ለምሳሌ በኮሪያ፣ በኮንጎ፣ በላይቤሪያ፣ በሶማሊያ ፣ ባደርፉር፣ በደቡብ ሱዳን ወዘተ።

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ለተባበሩት መንግሥታት ካበረከተቻቸው አበርክቶዎች አንጻር የሚገባትን ጥቅም አግኝታለች ለማለት ፈጽሞ የሚያስደፍር አይደለም። ይልቁንም ማህበሩ በተለያዩ ጊዜያት ከሕግ ውጪ በሆነ አግባብ ኢትዮጵያን ሲጨቁን ተመልክተናል። ለዚህም እንደማሳያ ከህዳሴው ግብድብ እና ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ ለውሳኔ ይሰበሰብባቸው የነበሩ ስብሰባዎች የቅርብ ጊዜ ትውስታዎች ናቸው። በእነኚህ መድረኮች አምባሳደር ታየ አጽቀስላሴ ያደርጓቸውን ተጋድሎዎች ማንም ኢትዮጵያዊ የሚረሳው አይደለም።

በእርግጥ ኢትዮጵያ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የተለያዩ ርዳታዎችን ታገኛለች። ነገር ግን ተደረጉ የተባሉ ርዳታዎች የእውነት የኢትዮጵያን ችግሮች የሚፈቱ ሳይሆኑ ኢትዮጵያ የምዕራባውያንን ርዳታ አንጋጣ እየጠበቀች ምዕራባውያን ከሚዘውሩት የኢፔሪያሊዝም ባቡር ላይ ብቻ እንድትሳፈር የሚያደርግ በአሳሪ ትብታቦች እና ችንካሮች የተሞሉ ናቸው።

የተባበሩት መንግሥታት የእውነት ኢትዮጵያ ከችግር እንድትወጣ የሚፈልግ ድርጅት ቢሆን ኖሮ የገንዘብ ርዳታ ከማድረግ ይልቅ እንዴት ገንዘብ ማግኘት ይቻላል? የሚለውን ባስተማረ ነበር ። ስንዴ ከመርዳት ይልቅ እንዴት ዘመናዊ እርሻን ማረስ እንደሚቻል ቢያሳየን ፣ የእርሻ መሣሪያዎችን ከመርዳት ይልቅ በቀላል ወጪ እንዴት የእርሻ መሣሪያዎች ሊሰሩ ይችላሉ የሚለውን ቴክኖሎጂ ማሳየት ይሻል ነበር።

ይህ አልሆነም ፣ሊሆን ይችላል ብሎ ማሰብም በብዙ መልመኩ የዋህነት እንደሚሆን ለማመን አይከብድም። ምክንያቱም ሁሌም በእነሱ ርዳታ ተንጠልጥለን እነሱ በዘረጉት ሃዲድ ብቻ እየሸመጠጥን እንድንኖር ስለሚፈልጉ ነው። የማርሻል ፕላን የዚህ ሁነኛ ማሳያ ነው።

ሶስተኛ ኢትዮጵያ በመሥራችነት ከምትታወቅባቸው ማህበር መካከል የአፍሪካ እግር ኳስ ማህበር አንዱ ነው። ለዚህ ማህበር መመሥረት ኢትዮጵያ ከማንም ሀገር የበለጠ አስተዋጽኦ ብታደርግም አሁን ላይ በዘርፉ ያለችበት ደረጃ የሚታወቅ ነው ። በርካታ የአፍሪካ ሀገራት ከኋላዋ ተነስተው ዛሬ ላይ የት እንደደረሱ ይታወቃል።

ሌላው ኢትዮጵያ ከመሠረተቻቸው ድርጅቶች መካከል የአፍሪካ ህብረት በግንባር ቀድምትነት ተጠቃሽ ነው። ይህ ድርጅት በኢትዮጵያ ፊትውራሪነት ተመስርቶ በርካታ የአፍሪካ ሀገራትን ከቅኝ ግዛት ነጻ ማውጣ ያስቻለ ድርጅት ነው። ነገር ግን ኢትዮጵያ ለዚህ ድርጅት ምስረታ እና ህልውና ካበረከተችው አብርክቶ አኳያ ምን ያህል ተጠቃሚ ናት ሲባል? መልሱ አጥጋቢ አይሆንም።

ኢትዮጵያ ካልጠቀስኳቸው አጅግ በርካታ ድርጅቶች ውስጥ በመሥራችነት እና በአባልነት ተሳትፋለች እየተሳተፈችም ትገኛለች። ነገር ግን በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት ኢትዮጵያ ለድርጅቶቹ ከምታበረክተው አብርክቶ አኳያ በቅጡ ተጠቅማለች ለማለት አያስደፍርም።

ከሰሞኑ የብሪክስ አባል ሀገር የሚያደርጋት አጋጣሚ ተፈጥሯል። ብሪክስ መግባቱ ብቻውን ትልቅ ነገር ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ኢትዮጵያ ካለፉት ስህተቶቿ ተምራ ከህብረቱ ማግኘት የሚገባትን ጥቅሞች ለይታ በዝርዝር በማስቀመጥ ጥቅሟን ማስከበር አለባት። ካልሆነ ግን ኢትዮጵያ ለሌሎች ፖለቲካል ኢኮኖሚ ኩነቶች የምታወጣቸውን የገንዘብ እና የጉለበት ወጪ ከመጨመር በቀር ምንም ጥቅም አይኖረውም።

እንደ ሀገር ካለፉ ችግሮቻችን በመማር በብሪክስ ብሔራዊ ጥቅሞቿን ለማስጠበቅ አንደኛ ተገማች እና ኢተገማች የሆኑ ዲፕሎማሲያዊ ሥራዎችን መፈጸም ይገባታል። ሁለተኛ ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም የነበሩ ዲፕሎማሲዊ ባህሎቿን ወይም አሠራሮች መቀየር ይጠበቅባታል ባይ ነኝ ። ሰላም!!

ዜና

# በኢትዮጵያ የመደጋገፍና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ መስፋፋትና ዘላቂ መሆን ይኖርበታል

## - ሚኒስቴሩ ከዘጠኝ ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ 13 የአቅመ ደካሞች ቤቶችን ገንብቶ አስረከበ

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ገጽታ ለመቀየር የመደጋገፍና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራን ዘላቂና መስፋፋት እንዳለበት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በ2014 ዓ.ም በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በጎርፍ የተጎዱ ቤቶችን በአዲስ መልክ ገንብቶ ለነዋሪዎች ባስተላለፈበት ወቅት ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል እንደገለጹት፤ እንደ አገር የበጎ ሥራዎችን ለማከናወን ባለፉት ዓመታት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ በሁሉም አካባቢዎች ሰፊ ሥራ እየተሠራ ነው። የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና በክልሎች ሰፊ ሥራ እያከናወነ ይገኛል። የኢትዮጵያን ገጽታ ለመቀየር የመደጋገፍና ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ ዘላቂ መሆንና መስፋፋት ይኖርበታል።

ሚኒስቴሩ ባለፉት የተወሰኑ ዓመታት በአዲስ አበባ ከተማ ከ52 በላይ የሚሆኑ መኖሪያ ቤቶችንና ሱቆችን ገንብቶ ማስረከቡን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያን ገጽታ ለመቀየር የመደጋገፍና ምርታማነትን የማሳግ ሥራ መስፋፋትና ዘላቂ መሆን አለበት ያሉት ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያን አገልግለው በእድሜ መግፋት ምክንያት አቅም ያጡ ወገኖች ማገዝ የሁሉም ሃላፊነት ሊሆን ይገባል ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ እንደ መንግሥት የተጀመሩ ሥራዎችን የበለጠ ማጠናከር፣ ሰላማችንን የበለጠ ማጽናት፣ እርስ በርስ መተባበርና የበጎነት ሥራዎችን ጥልቀትና መሠረት እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ ነው።

በመንግሥት የተጀመሩ ሥራዎች የኢትዮጵያን የመተባበርና የበጎነት ስሜት የሚያጠናክሩ ቢሆኑም ሁሉም በመተጋገዝ ባህልንና እሴትን ማጠናከር እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል።

እንደ አቶ መላኩ ገለጻ፤ ቀላል የሚመስሉ ችግሮች ተባብሰው የማይመለስ ጉዳት እንዳያደርሱ ጠንካራ የሆነ የቅድመ መከላከል ሥራ መሥራት፤ የጎርፍ አደጋዎችና ሌሎች ችግሮች ተባብሰው የሰው ሕይወትና ንብረት የማጥፋት ደረጃ ላይ እንዳይደርሱ በቅድመ መከላከል መንፈስ በመሥራትና የኢትዮጵያን አንድነትን አስጠብቆ መሄድ ያስፈልጋል። ፖለቲከኞች፣ መንግሥትና ሕብረተሰቡ በዚህ ጉዳይ ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይኖርበታል።

ከዓመት በፊት በደረሰ የጎርፍ አደጋ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ቤቶችን ከዘጠኝ ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ 13 ቤቶችን ገንብተን አስረክበናል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ከቤቱ መፍረስ በላይ በሰው ሕይወት ላይ የደረሰው አደጋ ያሳዝናል። የቤት የውስጥ ቁሶች በአንድ ጊዜ የሚሟሉ ባለመሆናቸው ወደፊትም መሰል ድጋፎች መቀጠል እንዳለባቸው ገልጸዋል።



አቶ መላኩ አለበል

በከተማ አስተዳደሩና በክልሎች የተጀመሩ የበጎ አድራጎት ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ። ለግንባታው በአይነትና በገንዘብ ድጋፍ ላደረጉ ባለሀብቶችም ምስጋና አቅርበዋል።

የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ አይዳ አወል በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ሐምሌ 2014 ዓ.ም በጎርፍ አደጋ የወደሙ ቤቶችን በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሙሉ ወጪ ተገንብተው ለነዋሪዎች መተላለፋቸው የመተጋገዝና የመደጋገፍ ተምሳሌት ነው። ክፍለ ከተማው ከከተማ አስተዳደሩ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በርካታ ሰው ተኮር ተግባራት አከናውኗል። በተለይ በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙ ነዋሪዎችን በመለየት የቤት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው። በበጀት ዓመቱ በርካታ ቤቶች በአዲስ መልክ ተሰርተውና ታድሰው ለነዋሪዎች ተላልፈዋል። ወደፊትም መሰል ድጋፎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ገልጸዋል።



## ሥልጠናው በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ያለውን የአገልግሎት ክፍተት የሚሞላ ነው

መስከረም ሰይፉ

አዲስ አበባ፡- በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሚሰጠው ሥልጠና በዘርፉ ያለውን የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተት የሚሞላ መሆኑን የካፒታል ሆቴልና ሥራ አመራር ኮሌጅ አስታወቀ።

ካፒታል የሆቴልና ሥራ አመራር ኮሌጅ እውቅና ባገኘባቸው የሆቴልና የቱሪዝም ዘርፍ ያሠለጠናቸውን ተማሪዎች ትናንት አስመርቋል።

ኮሌጁ በሆቴልና በቱሪዝም ዘርፍ ያሠለጠናቸውን ተማሪዎች ሲያስመርቅ ለስድስተኛ ጊዜ ሲሆን ዘንድሮም 115 ተማሪዎች በፍሮንት ኦፊስ ሱፐርቪዥን፣ በምግብና መጠጥ ቁጥጥር (ሱፐርቪዥን) ፣ በምግብ ፕሮዳክሽንና በምግብ አሠራር አሠልጥኖ አስመርቋል።

የሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያና የካፒታል ሆቴልና ሥራ አመራር ኮሌጅ ዋና ዲን ሰለሞን ታዬ እንደገለጹት ፤ ከፍተኛ ገቢ በሚያስገኘው የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ እንደ ሀገር ከፍተኛ የሆነ የተማረ የሰው ኃይል እጥረት አለ። ይህም ዘርፉ ዕድገት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ ይገኛል።

ለሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያዎች የሚሰጠው ሥልጠና ዓላማው የኢንዱስትሪው የአገልግሎት አሰጣጥ ክፍተትን ለመሙላት ያለመ ሊሆን ይገባል ያሉት አቶ ሰለሞን፤ ለዚህም በኮሌጁ የሚሰጡ ሁሉም ሥልጠናዎች ዓለም አቀፍ ደረጃውን ባሟላ መንገድ ነው ብለዋል።

ኮሌጁ በሆቴልና ቱሪዝም ማሠልጠኛ ዘርፍ በኢትዮጵያ ብቸኛው በባለ አምስት ኮከብ ደረጃ የራሱ የሆነ የማሠልጠኛ ሆቴል ያለው ተቋም ነው ። ይህም ሠልጣኞች ዓለም አቀፍ ቱሪስትን ለማስተናገድ የሚያስችል አቅም እንዲኖራቸው ያደርጋል ነው ያሉት።

አቶ ሰለሞን የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ በገበያ ላይ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው ሙያ መሆኑን ጠቅሰው፤ በየዓመቱ የሚያስተምሯቸው ተማሪዎችም ተፈላጊነታቸው ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

የካፒታል ሆቴልና ስፓ ሥራ አስኪያጅ አቶ ባንታየሁ ወልደሚካኤል ኮሌጁ ዓለም አቀፍ ደረጃን በጠበቀ መልኩ ሥልጠና እየሰጠ መሆኑን ገልጸው፤ ሰፊ የሰው ኃይል እጥረት ላለበት የሆቴል ዘርፍም እንደዚህ ያሉ ሥልጠናዎች ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል ብለዋል።

ኮሌጁ በዘርፉ ከ 6 ወር እስከ ሁለት ዓመት ጊዜ የሚፈጅ ሥልጠና የሚሰጥ ሲሆን የንድፈ ሃሳብ ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ በካፒታል ሆቴል ልምምድ እንደሚያደርጉና በቀጣይም ኮሌጁ በሚፈልገው መልክ ድጋፍ ማድረጉን እንደሚቀጥል ሥራ አስኪያጁ ገልጸዋል።

ከዚህ በተጨማሪም በኮሌጁ ለሚመረቁ ተማሪዎች በሆቴሉ ባሉ ክፍት የሥራ መደብ ቅጥር ይፈጸማል ብለዋል።

## ለመጪው በዓል ከተገዛው የምግብ...

ባቡሩ በበዓላት ወቅት የምግብ ዘይት ከጅቡቲ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲጓጓዝ በማድረግ ገበያውን የማረጋጋት ሥራ እያከናወነ መሆኑን ገልጸው፤ በዋናነት ሲያጓጉዛቸው የቆዩ የጭነት ዓይነቶች ኮንቴይነር፣ ማዳበሪያ፣ ስንዴ፣ ብረት፣ የምግብ ዘይት ይገኙበታል። በዚህ በጀት ዓመት ደግሞ የጭነት ተሽከርካሪዎችን ማጓጓዝ መጀመሩን ጠቁመዋል።

ባለፉት ጊዜያት የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ፣ የጸጥታ ችግር እና ባቡሩ በሚያልፍባቸው አካባቢዎች የግንዛቤ እጥረት ለአክሲዮን ማህበሩ ተግዳሮት ሆነውበት ነበር ያሉት ዶክተሩ፤ ችግሮቹን ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ ከፌዴራል ፖሊስ እና ከሀገር ሽማግሌዎች ጋር በመሆን መፍታት ተችሏል። ይህም የባቡሩን ዕቃ የማጓጓዝ አቅም አሳድጓል ሲሉ ገልጸዋል።

## በመዲናዋ በ6 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በሦስት አካባቢዎች ላይ እየተገነቡ ይገኛሉ ብለዋል።

የአያት ገበያ ማዕከል በሁለት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ወጪ በመገንባት ላይ ነው ያሉት አቶ ጉርሜሳ በሁለት ነጥብ አምስት ሄክታር መሬት ያረፈ ሲሆን ስድስት ብሎኮች አሉት ብለዋል።

ሰሚት ግብርና ምርቶች መሸጫ ገበያ ማዕከል ፕሮጀክት ሁለት ነጥብ ሦስት ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ መሆኑን ጠቅሰው በሁለት ነጥብ አራት ቢሊዮን ብር ወጪ በመገንባት ላይ መሆኑን ተናግረዋል።

በተጨማሪም በኮልፌ ገበያ ማዕከል ፕሮጀክት አንድ ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር በመገንባት ላይ መሆኑን ጠቅሰው በሁለት ነጥብ አንድ ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ግንባታ መሆኑን መሀንዲሱ አስረድተዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለያዩ መግቢያ አካባቢ በሮች ላይ በመገንባት ላይ የሚገኙት የግብርና ምርቶች መሸጫ ገበያ ማዕከላት ግንባታ ተጠናቆ በቅርቡ ወደ ሥራ እንደሚገቡም ሃላፊዎቹ ጠቅሰዋል።

## የባንኮችን የክፍያ ሥርዓት በማዘመን ዓለም...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ንግድ ባንክ ለኮርፖሬት ደንበኞች ሙሉ ለሙሉ የዲጅታል አገልግሎት ብቻ የሚሰጥበት ልዩ ዐቢይ ቅርንጫፍ በዋናው መሥሪያ ቤት አስመርቋል ።

በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ላይ የተገኙት የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ እንደተናገሩት መንግሥት ከሶስት ዓመት በፊት በጀመረው ሁሉን አቀፍ የፋይናንስ ሪፎርም መሠረት የፋይናንስ ተደራሽነትን ለማሳደግ በተወሰዱ ርምጃዎች ከፍተኛ ውጤቶችን ማስመዘገብ ተችሏል። የባንክ አገልግሎትና የክፍያ ሥርዓት በማዘመን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል። የባንክ አገልግሎት ቀድሞ መዘመን የተቀረውን ክፍለ ኢኮኖሚ በሚገባ ለማንቀሳቀስ አመቺ ሁኔታ የሚፈጥር ነው።

በባንክ ሥርዓት ውስጥ ሁሉም አገልግሎቶች ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረጉ፣ የደንበኞችን እንግልት ያስወገዱና ጊዜና ወጪ ቆጣቢ መሆን ይጠበቅባቸዋል ያሉት ሚኒስትሩ፤ የባንክና የህብረተሰቡ ግንኙነት የሠመረ ከሆነ በቀላሉ ኢኮኖሚው የሚያስፈልገውን ገንዘብ በመሰብሰብ ለታለመለት ዓላማ ማዋል የሚያስችል ይሆናል ብለዋል።

በዓለም ላይ በፈጣን ተለዋጭነታቸው ከሚታወቁ ዘርፎች መካከል የባንክ አገልግሎት ቀዳሚውን ሥፍራ እንደሚይዝ ገልጸው፤ ይህ የሚሆነውም ኢንዱስትሪው ከፍተኛ የሆነ የቴክኖሎጂ ግብዓት የሚጠይቅ በመሆኑ ነው። በመሆኑም ዓለም የደረሰበትን ደረጃ በየወቅቱ እየተከታተሉ መተግበር ይጠበቃል ነው ያሉት።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የጀመረው የለውጥ ሂደትም በዋናነት ደንበኞችን በተለያየ መስፈርት በመለየት ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግን መሠረት ያደረገ መሆኑን አመልክተው፤ አገልግሎቱ እንደ ሀገር ዲጅታል ኢትዮጵያን በ2025 እውን ለማድረግ ለተቀመጠው ግብ ትልቅ እገዛ እንደሚኖረው ገልጸዋል።

ይህ በአሁኑ ወቅት ለትላልቅ የኮርፖሬት ደንበኞች አገልግሎት ለመስጠት የተከፈተው ወረቀት አልባ ቅርንጫፍ፤ በቀጣይ በሀገሪቱ ሊስፋፋ የሚገባው ነው። ንግድ ባንክም ሆነ ሌሎች ባንኮች ይህንን እውን ለማድረግ ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የባንኩ ፕሬዚዳንት አቶ አቤ ሳኖ በበኩላቸው በቅርንጫፉ የሚሰጡትን አገልግሎቶች አስመልክተው እንደተናገሩት፤ ቅርንጫፉ ከመግቢያው ጀምሮ ደንበኞች የዲጅታል አሠራርን ተጠቅመው አገልግሎት የሚያገኙበት ነው። ካለማንም እገዛ «ቮቸር ማኔጅመንት ሥርዓት» በመጠቀም ራሳቸውን የሚያስተናግዱበት ይሆናል። በውስጡ ያሉትን የገንዘብ ማዘዋወሪያ ማሽኖችን በመጠቀምም የውጭ ምንዛሬ አገልግሎት፤ ገንዘብ ወጪና ገቢ ማድረግ ፤ ቼክ መመንዘርና ሌሎች አገልግሎቶችንም ማከናወን ይቻላል። አዲስ ሒሳብ ለሚከፍቱ ደንበኞችም በዲጅታል ሥርዓት ፎቶና ፊርማ ካለማንም እገዛ የሚቀበልም ነው።

ቅርንጫፉ ኢንተርአክቲቭ ቴለር በሚባል ማሽን አማካኝነትም ደንበኞች ከባንክ ባለሙያዎች አገልግሎት ማግኘት ሲፈልጉ በቪዲዮ የሚስተናገዱበት ሥርዓት ዘርግቷል። ቅርንጫፍ ባንኩ ነጻ የኢንተርኔትና ዋይ ፋይ አገልግሎት አለው። ይህንንም ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር የሚረዳ የኮምፒውተር ሥርዓት ተዘርግቶለታል። የቅርንጫፉ መከፈት ለታላላቅና ኮርፖሬት ደንበኞች የሚሰጠውን አገልግሎት ጥራት ከፍ ለማድረግ የሚያግዝ ሲሆን በዚህ አሠራር ረገድም አዲስ ምእራፍ የከፈተ መሆኑንም ፕሬዚዳንቱ ጠቁመዋል።

# በአርብ ማዕድ የማይተዋወቀውን የሚያሰባስቡት እናት



ስምስም መንግሥቱ

የአስፓልት መንገድ ለአካባቢ ገጽታ ምን ያህል ዋጋ እንዳለው የሚረዱት የተጎሳቆሉ መንደሮችን ገመና ሸፍኖ መያዙን ሲታዘቡ ነው። አስፓልቱን ተከትሎ የተለያዩ የንግድ ሱቆች ገጽታቸውን ለማሳመር የሚያደርጉት ጥረት አካባቢውን ይለውጠዋል።

ከንግድ ሱቆች ጀርባ ግን እጅግ የተጎሳቆሉ የመኖሪያ ቤቶች ይገኛሉ። ከሰሞኑ በአዲስ አበባ ከተማ ነባር ከሚባሉ ሰፈሮች አንዱ በሆነው ግንፍሌ ተብሎ በሚጠራው ሰፈር ተገኝተን ነበር። የአስፓልት መንገድ መኖሩ ብቻ ሳይሆን አካባቢው ለመኻል ከተማ ቅርብ መሆኑም ስለመንደሩ ሁኔታ እንዲያስቡ ያደርጋል።

በዚህ አካባቢ የሚኖረውን የቤተሰብ ብዛት፣ የአኗኗራቸውን ሁኔታ፣ ኑሮን ለማሸነፍ የሚያደርጉት ትግል፣ በአዕምሮዎ የተለያዩ ነገሮች እንዲመላለሱ ያስገድዳል። ወደዚህ መንደር ያቀናነው በምክንያት ነው። በገንዘቡ ምግብ ገዝቶ ለመመገብ በምግብ ቤቱ የተገኘ የማይተዋወቅ ሰው ተሰባስቦ በአንድ ማዕድ ቀርቦ ኪስ በማይጎዳ ዋጋ ተመግቦ የሚለያይበት ምግብ ቤት መኖሩን ሰምተን ለማረጋገጥ ወደ አካባቢው አቀናን።

ምግብ ቤቱ አካባቢ እስክንቃረብ ድረስ ምግብቤቱን የሚያውቀው ሰው ለማግኘት ተቸግረን ነበር። ወደ ምግብ ቤቱ የሚወስደውን መንገድ ከያዝን በኋላ ግን አመላካቹ ከነስሙ እየነገረን መርቶ አደረሰን። በአንድ ገበታ ማዕድ መቋደስ፤ «አፈር ስበላ፣ በሞቴ» ብሎ ቆሞ ለምኖ አንዱ ሌላውን ማጉረስ የኢትዮጵያውያን መገለጫ ነው። በቤተሰብ ደረጃ በትሪ፣ በተለይ ደግሞ በገጠሩ ቤተሰብ የሚመገበው ከስፌት በተዘጋጀ ሌማት ቀርቦ ነው። እንዲህ የቆየው በጋራ ተሰባስቦ የመብላት ባህል እየቀነሰ የመጣው ከጊዜ በኋላ እንጀራ ተቆርጦ ሰው በግሉ ሰሀን ይዞ መብላት ከጀመረ በኋላ ነው።

ይህ ሁኔታ ባለበት የማይተዋወቁ ቁጥራቸው እስከ 15 የሚደርሱ ሰዎች በጋራ ሆነው የሚመገቡበት ምግብ ቤት መኖሩ፣ በቆዩ መንደሮች በአነስተኛ ምግብ ቤት ውስጥ አገልግሎቱ መሠጠቱ ደግሞ ትኩረታችንን ሳበው። የጋራ ማዕዱ በሳምንት አንድ ቀን አርብ ብቻ ሲሆን፣ መስተንግዶውም ከቀኑ ስድስት ሰዓት ተኩል እስከ ስምንት ሰዓት ብቻ ነው።

በመንደሯ ውስጥ የምትገኘው አነስተኛ ምግብ ቤት የአርብ ደንበኞቿ ቁጥር እየጨመረ ስለሆነ በልተው ከጨረሱ ለተረኛ መልቀቅ እንጂ መቆየት አይቻልም። ምግብ ቤቷም ብትሆን በአንዴ ብዙ ሰው የማስተናገድ አቅም የላትም። የጎንና የቁመት ስፋቷን ለመለካት እንኳን ምቹ አይደለችም። እንደነገሩ መግቢያ እንድትሆን የተደረገች ናት። ከቤቱ ውጪ ለማስተናገድም አስፓልት ዳር በመሆኗ ምቹ አይደለችም። በአንደኛው ጎን በኩል ጎሚስታ ቤት፣ በሌላኛው ወገን ሌላ ንግድ ቤት መካከል የምትገኘው ምግብ ቤት እሙዬ ምግብ ቤት የሚል ስያሜ ተሰጥቷታል።

በእዚህ ቀን የምግብ ቤቱን ደንብ የማያውቅ ካልሆነ በስተቀር ለብቻው ገብቶ ምግብ የሚያዝ ደንበኛ የለም። ካለም ከሌሎች ተመጋቢዎች ጋር እንዲቀላቀል ይጠየቃል። ምናልባት ከተመጋቢዎቹ መካከል ሁለትና ሦስት የሚተዋወቁ ሊኖሩ ይችሉ ይሆናል እንጂ አብዛኞቹ ተመጋቢዎች አይተዋወቁም። ወንበር ስቦ መቀላቀል ነው። ባይተዋርነት የሚሰማው የለም። ለእዚያ ሰዓት ሁሉም ቤተሰብ ይሆናል።

አንዱ ቡድን በልቶ እስኪጨርስ ሌላው ቡድን መሥርቶ ተራ የሚጠብቅ ደንበኛ መኖሩን እኛም ምስክር ነን። ሁሉም በጋራ ተቋድሶ ክፍያውንም በጋራ በማዋጣት አሰባስቦ ክፍያ ፈጽሞ ለተረኛው ለቆ ይወጣል። በአንድ ጊዜ እስከ 15 ሰው ሆኖ የሚመገብበት ትሪ ስለመኖሩ እና ተመጋቢዎቹ ጠግበው ስለመብላታቸው እንዲሁም ዋጋውን በተመለከተም የተለያዩ ጥያቄዎችን ለማቅረብ ወደድን።

ጠግቦ መብላት የሚያሳስብ አለመሆኑን እና የቡድን ተመጋቢዎቹ በቃኝ ብለው ገበታው ከፍ እስኪል ድረስ ማባያው ወጥም እንጀራም የሚጨመር መሆኑን አረጋገጥን። የወጥ ዓይነቱም የተለያየ በመሆኑ ደንበኛው የፈለገውን ማስጨመር ይችላል። በጋራ የተመገቡት እያንዳንዳቸው የሚከፍሉት አንድ መቶ ብር ብቻ

**የማይተዋወቁ ቁጥራቸው እስከ 15 የሚደርሱ ሰዎች በጋራ ሆነው የሚመገቡበት ምግብ ቤት መኖሩ፣ በቆዩ መንደሮች በአነስተኛ ምግብ ቤት ውስጥ አገልግሎቱ መሠጠቱ ደግሞ ትኩረታችንን ሳበው**

መሆኑንም ሰማን።

ዋነኛዋ አስተናጋጅ የሚለብሱት ነጭ ማንገቻ ያለው ሽርጥ እና ነጭ የፀጉር መሸፈኛ ነው። ለአርብ ተመጋቢ ደንበኞቻቸው ገበታ በማዘጋጀት ሥራ ተጠምደዋል። ደርበብ ያሉት ጠይሟ ሴት ውበታቸው የሚስብ ሲሆን፤ ሁሉም እሙዬ ይላቸዋል። ውበታቸው በዕድሜ አልደበዘዘም። ሥራው እና የሚስተናገደው ሰው ቁጥር የቤት ጥበት ተደማምሮ ሙቀት እና ድካም የሚፈጥር ነበር። እርሳቸው ግን ገበታ ማዘጋጀቱን ተያይዘውታል። የሚያግዟቸው ሁለት ወጣቶች ባይኖሩ ኖሮ የእንጀራና የወጥ ጭማሪ የሚጠይቀውንና እግር በእግር የሚተካውን ደንበኛ ማስተናገድ ከባድ ነው። ደንበኛው የተፈቀደውን የመመገቢያ ሰዓት ለመጠቀም ይመስላል ፋታ አልነበረውም።

እኚህ ሴት የንግድ ትምህርት ሳይኖራቸው፣ ፈራ ተባ እያሉ የገቡበት ንግድ ዛሬ የአርብ ማዕድ ፈጠራን ተጠቅመው ደንበኞችን ማፍራት አስችሏቸዋል። ለዓይናችን ያነሰችውን ምግብ ቤት እርሳቸው ግን ከየትኛውም ምግብ ቤት በላይ አግዝፈው ያይዋታል። የኑሮ ውጣ ውረድ በገጠማቸው ጊዜ ችግራቸውን ለመወጣት መላ ስለሆነችላቸው ትልቅ ደረጃ ላይ እንደደረሱ ይቆጥሩታል። ትርፍን ታሳቢ አድርገው ሳይሆን ዛሬም የዕለት ኑሮን ማሸነፍ ዓላማ አድርገው እየሠሩ ነው።

በንግድ ዓለም አትርፎ ለውጥ ማምጣት ወይም ማደግ ግድ ነው። እርሳቸው ግን በተቃራኒው በጎነት፣ አብሮነት፤ በጋራ የመብላት ባህልንም አስጠብቆ ሰዎችን ማቀራረብና ማስደሰት፣ ከደንበኛ ፍቅር ማግኘት ቅድሚያ የሚሰጡት ጉዳይ ነው። እሙዬ በኑሯቸው ስላጋጠማቸው ውጣ ውረዶች፣ ስለንግድ ሥራቸውም መነሻ እንዳጫወቱኝ፣ «እሙዬ» ልጆቻቸው ያወጡላቸው ስም ነው። ደንበኞቻቸውም እንደልጆቻቸው እሙዬ ብለው ስለሚጠሯቸው ቤተሰባዊነት ይሰማቸዋል።

እሙዬ ብሎ የሚጠራቸው ሰው ብዙ በመሆኑ ትክክለኛውን መጠሪያቸውን ዙሪያሽወርቅ አበጋዝ የሚለውን የሚዘነጉበት አጋጣሚ መኖሩን ያስታውሳሉ።ወይዘሮ ዙሪያሽ እንዳጫወቱኝ ውልደታቸውና እድገታቸው ደሴ ዙሪያ ኩታበር ወረዳ ውስጥ ነው። ወላጅ እናታቸው ኑሮአቸውን አዲስ አበባ ከተማ በማድረጋቸው ያደጉት በአያቶቻቸው እጅ ነው። የሚጠሩትም በእናታቸው አባት በአያታቸው ስም ነው።

ደሴ የቆዩት 7ኛ ክፍል እስኪደርሱ ብቻ ነበር። ከዚያ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ከተማ መጥተው ከእናታቸው ጋር ኖሩ። በወቅቱም የ12 አመት ታዳጊ ይሆናሉ። እናታቸው ግንፍሌ አካባቢ ካታንጋ ተብሎ በሚጠራ መንደር ውስጥ ይኖሩ ነበር። አሁን የሚኖሩበት ግንፍሌ አካባቢ የመጡት ትዳር ከያዙ በኋላ ነው።

ወደ አዲስ አበባ ከተማ ለመምጣት ምክንያት የሆናቸው በወቅቱ በነበረው ወታደራዊ የደርግ ሥርዓት በየቀበሌው የኪነት ቡድን ተቋቁሞ የሙዚቃ ሥራዎች ይሠሩ ነበር። ብዙ ወጣቶችም ኪነት ውስጥ በመግባት ጊዜያቸውን ያሳልፉሉ። በዚህም ከትምህርት ገበታቸው የሚስተጓጎሉ ነበሩ። የወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ እናትም ልጃቸው ኪነት ውስጥ ገብታ ትምህርቷን ታቋርጣለች የሚል ስጋት ስላደረባቸው አጠገባቸው እንድትሆን መረጡ። ወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ ግን እናታቸው ቤት ሲመጡ የጠበቃቸው እንጀራ አባት ነበር።

ወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ «እንጀራ አባትን አባባል ነው።» ይላሉ። ሲያሳድጓቸው እንደአባታቸው ያዩዋቸው ነበር። ደሴ እያሉ አልፎ አልፎ አዲስ አበባ ከተማ ይመጡ ስለነበር ቅርበታቸው ከልጅነት ጀምሮ ነው። አብረው የኖሩት መልካም አባት ሆነው ነው። አዲስ አበባ ከመጡ በኋላም የከፋቸው ነገር ባይኖርም ተወልደው ላደጉበት ደሴ ልዩ ፍቅር አላቸው። ከጓደኞቻቸው ጋር ቦርከና ወንዝ ላይ መዋኘታቸው እና ጨዋታው ጥሩ ትዝታ ነው።

ወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ ኑሮአቸውን አዲስ አበባ ከተማ ካደረጉ በኋላም ቢሆን ከአካባቢያቸው ጋር ተላምደው ለመኖር አልተቸገሩም። ትምህርታቸውን በመቀጠል በላይ ዘለቀ ትምህርትቤት እስከ 8ኛ ክፍል፤ 9ኛ እና 10ኛ ክፍልን ደግሞ በዳግማዊ ምኒልክ፣ የ11ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ደግሞ ምሥራቅ አጠቃላይ ትምህርት ቤት ተማሩ። በትምህርታቸው ጎበዝ ከሚባሉት ተማሪዎች መካከል ይጠቀሳሉ።

እርሳቸው በተማሩበት ዘመን ለ9ኛ እና 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ይሰጥ የነበረው ትምህርት የሂሳብ መዝገብ አያያዝ (አካውንቲንግ) የሚባለው ስለነበር እርሳቸውም እዚህ ደረጃ ለመድረስ ጠንካራ ተማሪ ለመሆን ጥረት አድርገዋል።በተለይ ደሴ ኩታበር ትምህርት ቤት ከታናሽ ወንድማቸው ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ አብረው ሲማሩ በመካከላቸው የነበረውን ፉክክር አይረሱትም።

ሌሎች የክፍሉን ተማሪዎች ለመብለጥ ሳይሆን የሚፎካከሩት ወንድማቸውን ነበር። በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች እኩል ውጤት ያገኙ ነበር። የሚለያዩት በሁለት የትምህርት ዓይነቶች ነው። ወንድማቸው በእንግሊዝኛ ትምህርት ይበልጣቸዋል። እርሳቸው ደግሞ በአማርኛ ጎበዝ ተማሪ ናቸው። በእህትና ወንድም መካከል የነበረውን ፉክክር ያዩ መምህራኖቻቸው አንድ ክፍል ውስጥ እንዳይማሩ አድርገው ነበር።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## በአርብ ማዕድ የማይተዋወቀውን...

ከገጽ 6 የዞረ

ወንድማቸውን የሚበልጧቸው በ11 ወር ነው።ወንድማቸው ትምህርት ቤት ካልገባ አልማርም ማለታቸውንም ያስታውሳሉ። ሁለቱም በትምህርታቸው በያዙት ጥንካሬ እንዳይቀጥሉ በየቀበሌው የተቋቋመው ኪነት ቡድን እንቅፋት ሆነባቸው። ወንድማቸው ኪነትን ሽሽት ወደ እምነት ተቋም ገቡ። በወቅቱ ኪነት ውስጥ ያልተሳተፈ ወጣት መንገላታት ይደርስበት ነበር።

አስገዳጅነቱ ቤተሰብንም እስከማሰር የደረሰ ስለነበር፤ በፍራቻ እርሳቸው ለተወሰነ ጊዜ በኪነት ውስጥ አሳልፈዋል። በኪነት ውስጥ ተወዛዋዥ ሆነው በደሴ ዙሪያ እየተዘዋወሩም በተለያዩ መድረኮች የቅስቀሳና የማዝናናት ሥራ ሠርተዋል። በኪነቱ ደሴና አካባቢዋን በደንብ ማወቅ ችለዋል። ልጅነትም ስለነበር ጭፈራው ያስደስታቸው ነበር። ኪነቱ በትምህርታቸው ውጤት ላይ ተጽእኖ አሳድሯል።እናታቸው አዲስ አበባ ከተማ አጠገባቸው እንዲሆኑ የወሰኑት ለዚህም ነው ።

ኑሮአቸውን አዲስአበባ ከተማ ካደረጉ በኋላም በትምህርታቸው ከ11ኛ ክፍል በላይ አልዘለቁም። ወንድማቸው ግን ለጊዜው ከቆዩበት የእምነት ተቋም ወጥተው የቀለም ትምህርታቸውን ቀጥለው ሕክምና ተምረው ሀኪም ሆነዋል። አሁን ያሉት እንግሊዝ ሀገር ነው። እርሳቸው ግን ከ11ኛ ክፍል በላይ ያልዘለቁት የፍቅር ጓደኛ በመያዛቸው ነው። ጓደኝነቱም ወደ ትዳር የተለወጠው በአጭር ጊዜ ነበር።

ወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ እንደነገሩን፤ አሁን የትዳር አጋራቸው ከሆኑት ጋር የፍቅር ግንኙነቱ የተጀመረው በዚያው በሚኖሩበት አካባቢ ነው። ባለቤታቸው ደግሞ ያኔ ከራሺያ ትምህርታቸውን ጨርሰው ገና መምጣታቸው ነበር። ይህ የሆነው በ1977 ዓ.ም ነው። የጓደኞችም ግፊት ገብቶበት፤ እነርሱም ተፈላልገውና ተዋድደው ወደትዳር ገቡ። ወደ ትዳር ሲገቡ ሠርግ አልነበረም። አብረው መኖር እንደጀመሩ ልጅም ቶሎ በመምጣቱ ለትምህርት ጊዜ አልነበረም። ባለቤታቸው ሥራቸው ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪ መሆኑ ደግሞ የበለጠ ከትምህርት እንዲርቁ አደረጋቸው።

ባለቤታቸው የተማሩት የሥጋ ቴክኖሎጂ ስለነበር ወንዶገነት ውስጥ በሚገኝ የሥጋ ፋብሪካ ውስጥ በኃላፊነት ሥራ አገኙ። ባለቤታቸውን ተከትለው መሄድ ግድ ስለነበር የስድስት ወር ልጃቸውን ይዘው ኑሮአቸውን በወንዶገነት አደረጉ። የሚኖሩት ፋብሪካው ባመቻቸላቸው መኖሪያቤት ውስጥ ነበር ። ባለቤታቸውም ኃላፊ ስለነበሩ የተለየ ቦታ ይሰጣቸው ነበር።

የአካባቢው ማኅበረሰብም አክብሮትና ፍቅር ይሰጣቸው ስለነበር በኑሮአቸው ደስተኛ ነበሩ። እርሳቸውም ቢሆኑ በተለይም ሁለተኛ ልጃቸውን በወለዱበት ወቅት በአካባቢው ማኅበረሰብ እንክብካቤ ታረሱ። ቤታቸው ለመጣው ሁሉ ክፍት ነበር። የሚሸኙት አብልተውና አጠጥተው ነው። ባለቤታቸው ኃላፊም ቢሆኑ የሚያሳልፉት ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር ግን እንደማንኛውም ኅብረተሰብ አብሮ ነበር። በዚህም በአካባቢው ላይ ይወደዳሉ። በኑሮአቸው ደስተኛ ነበሩ። ስለኑሮ አይጨነቁም።

በዚህ ሁኔታ ወንዶገነት ውስጥ የቆዩት ለሰባት አመት ነው። ባለቤታቸው ሥራ ቀይረው ወደ ኮምቦልቻ ሄዱ። ወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ ግን ባለቤታቸውን ተከትለው አልሄዱም። እናታቸው ታመው ስለነበር ወደ አዲስ አበባ ከተማ ተመለሱ። የሕይወት ውጣ ውረድ የተጀመረው እዚህ ላይ ነው ይላሉ።

ወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ፤ እርሳቸው እንዳሉት እናታቸው ከሕመማቸው ፈውስ ሳያገኙ አረፉ። ኀዘናቸውን ጨርሰው ባለቤታቸው ጋር ኮምቦልቻ ሄዱ። ሆኖም ግን የአካባቢው የአየር ፀባይ ስላልተመቻቸው ከአንድ አመት በላይ መቆየት አልቻሉም። ወደ አዲስ አበባ ከተማ ተመለሱ። ባለቤታቸውም ሥራ ቀይረው የሄዱበት መሥሪያቤት ውስጥ ጥሩ ነገር አልገጠማቸውም። ሆኖም ግን ለአምስት አመት ያህል በሥራ ኮምቦልቻ ቆይተዋል።

ነገሮችን ምቹ እንዳይሆን ያደረገው አንዱ ምክንያት የመንግሥት ለውጥ ነበር። ወታደራዊው የደርግ አገዛዝ ሥርዓት በሕዝባዊ ወያኔ(ሕወሓት) የተቀየረበት የሽግግር ጊዜ ስለነበር መረጋጋቶች አልነበሩም። በተለይም ባለቤታቸው በሚሠሩበት መሥሪያ ቤት ውስጥ የነበረው የሥራ ግምገማ ምቾት አልሰጣቸውም። በኋላም ከሥራ ታገዱ። በአጋጣሚ አዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት የሥራ ማስታወቂያ አውጥቶ ነበር። ባለቤታቸው ከኮምቦልቻ ባይመለሱም እርሳቸው ማስታወቂያው እንዳያልፋቸው አስፈላጊ ሰነዶች ይዘው ለተቋሙ ያለውን ሁኔታ በማስረዳት ማመልከቻውን እንዲቀበሏቸው አደረጉ። ሥራውም ተሳክቶ ገብተው ለብዙ አመት ማገልገል ችለዋል። ይሁን እንጂ ይሄም ድርጅት ባላወቁት ምክንያት ከሥራቸው አሰናበታቸው።

ወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ ባለቤታቸውን በሥራ ትጋታቸው ያልተነገረላቸው ናቸው ይሏቸዋል። በተለይ ቄራዎች ድርጅት ላይ ሽታን የሚያስወግድ ፈጠራ ተግባራዊ በማድረግና በድርጅቱ ውስጥም ብዙ ለውጥ እንዲመጣ በማድረግ በሥራ መትጋታቸውን መስክረውላቸዋል። የሥራ ትጋታቸውን ያህል ምስጋና አለማግኘታቸውን በቁጭት ይናገራሉ። ‹‹እሱ አፍ አውጥቶ ስለራሱ መናገር ባይችልም እኔ አፍ ልሆንለት እችላለሁ›› በማለት መስክረውላቸዋል።

ወይዘሮ ዙሪያሽወርቅም የራሳቸውን ገቢ ለመፍጠር የተንቀሳቀሱት ባለቤታቸው በሥራቸው ላይ ደስተኛ አለመሆናቸው እየገባቸው ከመጣ በኋላ ነበር። ለባለቤታቸውም ‹‹ከዚህ በኋላ ወደ ሥራህ ብትመለስም ባትመለስም እኔ ልጆቼን አሳድጋለሁ›› ይሏቸው ነበር። አሁን ምግብ ቤት ያደረጉት የባለቤታቸው ቤተሰቦች ባወረሷቸው መኖሪያቸው ባደረጉት ቤት ውስጥ ነው።

የመጀመሪያ የገቢ ምንጭ አድርገው የጀመሩት ባልትና ነበር። ነገር ግን አዋጭ ሆኖ አላገኙትም። ሌላ ሥራ አሁን ‹‹ ቡና ጠጡ›› እንደሚባለው የጀበና ቡና በአንድ ብር ከሃምሳ ሳንቲም መሸጥ ጀመሩ። ይህን ምክር የሰጣቸው ጎረቤት ነበር። ሥራውን የጀመሩ ቀን በአጋጣሚ ብዙ ሰዎች ደንበኞች ነበሩ። በወቅቱ ከመፍራታቸው የተነሳ እንደመሸሽም ብለው ነበር። በዕለቱም ከሽያጩ 27 ብር አገኙ። የመጀመሪያ ልጃቸው ግን ተቃውማቸዋለች። በተደጋጋሚ በር በመዝጋት ሥራቸውን እንዲያቆሙ ታደርግ ነበር። ከልጃቸው ጋር እየታገሉ ሥራውን ቀጠሉበት።

ቡና መሸጡን እንደ ንግድ አዩት እንጂ ቀድመው እንጀራ ጋግረው ይሸጡ ነበር። ያኔ የአንድ እንጀራ ዋጋ 60 ሣንቲም ነበር። በዚህ ዋጋ የሚሸጡት አንድ ኩንታል ጤፍ በ120ብር እየገዙ ነው። በዚህ ሁኔታ ደስተኛ ሆነው ገቢ እያገኙ የባለቤታቸውን እጅ ሳይጠብቁ ኑሮአቸውን መምራት ጀመሩ። ባለቤታቸውም ያበረታቷቸው ነበር። በዚያን ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለውን ላቀች የተባለውን ምጣድም ገዝተው ሰጧቸው። የመንደሩ ሰውም በተከሉት ምጣድ እየተገረሙ የተለያየ አስተያየት ይሰጧቸው ነበር።

በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ ሦስተኛ ልጃቸውን ፀነሱ። ጽንሱ እያደረገ ሲሄድ አቅም አነሳቸው። ሳጠራ ከልለው እንጀራ እየጋገሩ የሚሸጡባትን ቤት በ40 ብር አከራይተው መጠቀም ጀመሩ። ኪራዩ በሂደት 100 ብር ደርሶ ኑሮአቸውን መደጎም ቻሉ።

በአንድ ወቅት ባለቤታቸው ኃላፊ ሆነው ስለኑሮ የማይጨነቁ የነበሩ ሴት እንጀራ ጋግረው መሸጥ ሲጀምሩ የሚኖረው ስሜት ከባድ እንደሚሆን ይገመታል። ወደ ቀጣዩ ጨዋታችን ሳንገባ ስሜታቸውን ጠየቅናቸው። የሥነልቦና ዝግጅት እንደነበራቸው ነገሩን። እርሳቸው እንዳሉት ከባለቤታቸው ጋር ስለሥራም ሆነ ስለማንኛውን ነገር በግልጽ የመነጋገርና የመወያየት ልምዱ ስላላቸው ሁሉንም ነገር ያውቃሉ። ስለሥራቸውም ይነግሯቸው ከነበረው ሁኔታ አንድቀን ችግር እንደሚያጋጥማቸው የሚጠብቁት ጉዳይ ነበር።

እርሳቸው ሥራ የላቸውም። ልጆቻቸውም ገና ሕፃናት ናቸው። ስለዚህ ጠንክረው መወጣት እንዳለባቸው ሁሌም እራሳቸውን ዝግጁ ያደርጉ ነበር። ችግሩ ሲያጋጥማቸውም አዲስ አልሆነባቸውም። እንጀራ ጋግረው ለመሸጥ ለውሳኔ ያልተቸገሩት ለዚህም ነው።

በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት ይሠሩበት የነበረውን ቤት ቢያከራዩም ከአራስ ቤት ሲነሱ ያከራዩትን ቤት አስለቅቀው ቡና መሸጡን ተያያዙት። አካባቢያቸው የሚገኘው የስዕል ትምህርት ቤት ተማሪ ደንበኞች ቡናው

> **በንግድ ዓለም አትርፎ ለውጥ ማምጣት ወይም ማደግ ግድ ነው። እርሳቸው ግን በተቃራኒው በጎነት፣ አብሮነት፤ በጋራ የመብላት ባህልንም አስጠብቆ ሰዎችን ማቀራረብና ማስደሰት፣ ከደንበኛ ፍቅር ማግኘት ቅድሚያ የሚሰጡት ጉዳይ ነው።**

ከቁርስ ጋር እንዲቀርብላቸው ሀሳብ አቀረቡላቸው። በደንበኞቻቸው ሀሳብ ተስማምተው ለቤታቸው ከሚጠቀሙት በርበሬና እንጀራ ቁርስ ማቅረብ ጀመሩ። ያኔ አንድ ፍርፍር የሚሸጡት 12 ብር ነበር።

ወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ የቡና ንግዱ አንድ ዕድል አስገኘላቸው። ከስዕል ትምህርት ቤት ደንበኞች መካከል ምህረት የምትባል ሰዓሊ ዕድሉን አመቻችችላቸው። ሰዓሊ ምህረት የዶክትሬት ትምህርት በምትከታተልበት ቪየና ሀገር በተዘጋጀ የኢትዮጵያን ቡና በሚያስተዋውቅ ፌስቲቫል ላይ እንዲካፈሉ አመቻችችላቸው። በዕድሉ ተጠቅመው ለ15 ቀናት በቪየና ሀገር ቆይታ አድርገዋል። የኢትዮጵያን ቡና አስተዋውቀው፣ በመስተንግዶአቸው አድናቆትም አግኝተው ገንዘብም ይዘው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ።

እግር ከሀገር ሲወጣ መቅረትን የመመኘት ነገር አለ። ወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ የነበራቸውን ስሜት ጠየቅናቸው። አንዳንድ ሆቴል ቤት ያላቸው እነርሱ ጋር እንዲሠሩ ጥያቄ ቢያቀርቡላቸው እንኳን መቅረት እንዳልፈለጉ ነገሩን። ‹‹በሀገሬ ሠርቼ መለወጥ እየቻልኩ ለምን በሰው ሀገር ለሌሎች አገልጋይ እሆናለሁ። ጠንክሬ ከሠራሁ በሀገሬም መለወጥ እችላለሁ። አሁንም በሥራዬ ለውጥ እያመጣሁ እገኛለሁ።›› አሉን። በቪየና የነበራቸው አጭር ቆይታ ቢሆንም ከኢትዮጵያውያን ጥሩ አክብሮትን አግኝተው የሥራ ባህልንም ልምድ እንዳገኙበት አጫውተውናል። ኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝ ባይከሰት ኖሮ ቪየና የመመላለስ ዕድልም እንደነበራቸው ገልጸውልናል።

ወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ በሥራቸው አጋጣሚ ያገኙት ከሀገር የመውጣት ዕድል ሥራቸው ላይ የበለጠ ጠንካራ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። በሥራ ያፈሯቸው ደንበኞች ቤተሰብ ሆነው ለእርሳቸው እድገት ተባባሪያቸው ሆነው አገኟቸው።እርሳቸው እንደሚሉት ለትርፍ ብለው ቢንቀሳቀሱ ውጭ ሀገር ድረስ እስከመውሰድ የሚደርስ ደንበኛ እያተረፉም ነበር። ከደንበኞቻቸው ያገኙትን ፍቅር በገንዘብ እንደማያገኙ ነገሩን። ‹‹አንቺ ካልተለወጥሽበት ‹የምትሠሪው ለነፍስሽ ነው ለስጋሽ› የሚሉኝ ሰዎች አሉ። እኔ ግን የምሠራው ለሁለቱም ነው ብዬ አስባለሁ። መለወጥ መኪና መግዛት፣ ፎቅ ቤት መሥራት ብቻ አይደለም። በማገኘው ገቢ ቤተሰቤን እያስተዳደርኩ ነው። ግብርም እከፍላለሁ። በሥራዬ ደስተኛ ነኝ። ከዚህ በላይ ምን እፈልጋለሁ?›› ይላሉ። ታማኝነት፣ አመስጋኝነት ከሰዎች ፍቅር ማትረፍ ለእርሳቸው ትልቅ ቦታ አለው።

አንዳንዶች እንደሚያደርጉት እንዲህ የደንበኞችን ፍቅር ያተረፉት በምግብ ዝግጅት እና በንግድ ክህሎት ሰልጥነው አይደለም። ስለሙያቸውም ደንበኞቻቸውን ምስክር ያደርጋሉ። አጋጣሚም ቪየና እንዲሄዱ ያመቻቸችላቸውን ደንበኛቸውን አመስግነዋታል።

ቡናው ቁርስ እንዲኖረው ከደንበኛው በቀረበላቸው ሀሳብ የፍርፍር ቁርስ በየዓይነቱ ምሳ አዘጋጅቶ ማቅረብ ተጀመረ። በሂደት ደግሞ የማይተዋወቁ ሰዎች በጋራ ሆነው የሚመገቡት የአርብ ማዕድ ተጀመረ። ይሄም ሀሳብ ከስዕል ትምህርት ቤት ደንበኞቻቸው የመጣ ነው። አንዳንዴ ከትምህርት ቤቱ ትእዛዝ ሲኖራቸው ሰፋ ባለ ሁኔታ ያቀርባሉ። ይህ አጋጣሚ ወደ አርብ ማዕድ እንዲያመሩ አደረጋቸው። ከትምህርት ቤቱ ደንበኛቸው ምህረት የምትባለው ሱዳን ሀገር በሄደችበት ወቅት አንድ ትልቅ ትሪ አመጣችላቸው።

በትሪው በጋራ ማዕድ የቀረቡትም እነዚሁ የስዕል ትምህርትቤት ደንበኞቻቸው ነበሩ። ለሌሎች የማስተዋወቁንም ሚና የተወጡት እነዚሁ ደንበኞቻቸው ናቸው። በሂደት እየተለመደ እውቅና ደረጃ ደርሷል። በአንድ ወቅት በእንግድነት ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የጎበኛቸው አንድ ሰዓሊ የሱዳን ዜጋ ሁለት ትሪ በስጦታ አበረከተላቸው። አሁን የአርብ ማዕድን ለደንበኞቻቸው እያቀረቡ የሚገኙት በእነዚህ ሦስት ትሪዎች ነው።

ከቀኖች ሁሉ አርብ የተመረጠበትን ምክንያትም ወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ እንደነገሩኝ የፆም ምግብ የተለያየ እምነት ተከታይ የሆነውን ሁሉ የሚያሳትፍ በመሆኑ ነው። ተመጋቢው ጥርጣሬ ሳይኖረው ይመገባል። በአርብ ማዕድ ዘጠኝ ዓይነት ወጥ ይቀርባል። እንጀራውም ትሪው የሚቻለውን ያህል ይዘጋጃል። ጭማሪውም የሚቆመው ደንበኛው ጠግቦ መርቆ ሲነሳ ነው። በዕለቱ የሚመጣውን ደንበኛ አስተናግዶ አስደስቶ ለመሸኘት በሥራ ተጠምደው ስለሚውሉ የእንጀራውም ሆነ የወጡ ጉዳይ አያሳስባቸውም።

ወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ እርሳቸው እንደሚሉት ከትንሽ ተነስተው አሁን ላይ የደረሱት ከ14 አመት ድካም በኋላ ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥም ከፍ አድርገው የሚናገሩት ፍቅር፣ መተሳሰብን፣ አንድነት ያዩበት እንደሆነ ነው። በተለይ ደግሞ የአርብ ማዕድ በእጅጉ አስደስቷቸዋል። ይሄ በአንድ ላይ መብላት አድጎ፣ አንድ ሰው ወገኑ ሲጎዳ ለወገኑ የሚደርስ፣ የሚያስብ፣ የሚቆረቆር እንዲሆን ይፈልጋሉ። አብሮ ማደግና መለወጥ እንዲጎለብት ይሻሉ።

ይህን ፍላጎታቸውን ለማሳካት አቅማቸው እስከፈቀደ ድረስ እንደማያቋርጡ ወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ ይገልፃሉ። የሚቀጥለውን ጉዞአቸውንም ፈጣሪ ያውቃል ይላሉ። ወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ አራት ልጆች አፍርተዋል። ሁለቱ ልጆቻቸው ትዳር ይዘው የልጅ ልጆች አሳይተዋቸዋል። ሁለቱም የራሳቸው መተዳደሪያ ፈጥረዋል።

በዚህ ሥራቸውና በኑሮ ውጣ ውረድ ልጆቻቸው፣ ሌሎችም ከእርሳቸው የሚማሩት ተሞክሮም ወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ እንዲህ ገልጸውልናል። ‹‹ሰዎች ገንዘብን ከማስቀደም ሰው ማትረፍ ላይ ቢሠሩ ደስ ይለኛል። እኔ ይሄን በማድረጌ ተጠቅሜያለሁ። ሰው ለመሥራት ዝግጁ ከሆነ ፈጥሮ መሥራት የሚቻል ብዙ ነገር አለ። ከስረው ይስሩ እያልኩ አይደለም። በተለይ ቤት ተከራይተው ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ወጪ ስላለባቸው ድካማቸውንም ወጪያቸውንም የሚሸፍን ነገር ማግኘት አለባቸው። የምቃወመው ግን ሌላውን ጎድቶ ትርፍ ለማግኘት የሚደረገውን ጥረት ነው።›› ሲሉ ሀሳብ ሰጥተዋል።

የኑሮ ውጣ ውረድ ወደ ምግብ ሥራ ያስገባቸው እኚህ እናት አዛኝነታቸውን፣ መልካምነታቸውን፣ ደስታቸውን፣ የመንፈስ ጥንካሬያቸውን ገጽታቸውም ይናገራል። ምንም እንኳን በ14 አመት የድካም ጊዜ ምግብቤታቸው ወደ ሆቴል ቤት ባይለወጥም ተስፋ አለመቁረጥን አይተንባቸዋል። የኑሮ ውድነት ጉዳይ በሰፊው እያነጋገረ ባለበትና እምነትም በመነመነበት በዚህ ወቅት እንዲህ ያሉ ሰዎችን ማግኘት በእጅጉ ያስደስታል። እንዲበዙም ያስፈልጋል። ከእኚህ እናት መልካም የሆነ ተሞክሮ ለመቅሰም ዝግጁ የሚሆኑ ሰዎች እንደሚኖሩ ተስፋ እናደርጋለን።

ከወይዘሮ ዙሪያሽወርቅ ጋር በነበረኝ ቆይታ በምግብ ቤቱ ግድግዳ ላይ የተሰቀሉትን ምስሎች ስንቃኝ የሰዓሊ እጅ ጥበብ ያረፈበት የስዕል ውጤት አየን። የስዕል ትምህርትቤት ደንበኞች ዐሻራ በእሙዬ ምግብቤት ውስጥ በብዙ እንዳረፈበት ለማስተዋል ችለናል። ቪየና ሀገር በነበሩ ጊዜ ቡና ሲያስተናግዱ ምስላቸውን የያዘ በፖስተር መልክ የተዘጋጀ በግድግዳው ላይ ተሰቅሏል። ስለእርሳቸው የደከሙ ሰዎች ያደረጉላቸውን ውለታ ማስታወሻ በታሪክ መያዛቸውም ያስመሰግናቸዋል። የእኚህን ታታሪ እናት ትጋትና ጥረት የሚቆጥርላቸው ጊዜ እንዲመጣላቸውና ጤና ሰጥቷቸው በበለጠ ከፍ ብለው እንድናገኛቸው እኔም ተመኝቼ ተሰነባበትን።

# ባህልና ቱሪዝም

## ለከተማዋ ቱሪዝም ተጨማሪ አቅም እንደሚሆን የሚጠበቀው ማኅበር

**ዳግም ከበደ**

ኢትዮጵያ የበርካታ ባህል፣ ታሪክ፣ መልክዓ ምድርና ተፈጥሮ፣ አርኪዮሎጂካልና የሥነ ሕንፃ ጥበብ እንዲሁም የአያሌ ቅርሶችና መስህቦች ባለቤት ነች። እነዚህ የቱሪዝም ሀብቶች ሀገሪቱን በዓለም ካሉ ታሪካዊና ቀደምት ሀገራት ተርታ የመጀመሪያዋ ያደርጋታል። የቱሪዝም በረከቶቹን በአግባቡ ማስተዋወቅ መጠበቅና ማልማት ከተቻለም የኢኮኖሚ አቅምንና የሀገር ገፅታን ለመገንባት ሁነኛ አማራጭ እንደሆነ የዘርፉ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ።

የኢትዮጵያ መንግሥትም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለዘርፉ ልዩ ትኩረት በመስጠት ከዋና ዋና የኢኮኖሚ ምሰሶዎች ተርታ መድቦታል። የግሉ የቱሪዝም ዘርፍ አንቀሳቃሾችም የዚህ እቅድ ዋንኛ ተዋንያን በመሆናቸው በትብብርና በቅንጅት ከመንግሥት ጋር እንዲሠሩ ይጠበቃል።

የቱሪዝም ባለሙያዎች ዘርፉ ቀጣይነት ያለው ልማትን፣ ተከታታይ የገበያና ማስተዋወቅ ሥራን ፣ ዘመናዊ የሆስፒታሊቲና አገልግሎት አሰጣጥ፣ የአስጎብኚዎችና ቱር ኦፐሬተርስ ቅንጅትን እንዲሁም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን እና የግሉ ዘርፍ ትብብርን እንደሚጠይቅ ይናገራሉ። በተለይ ከትብብር፣ ከመናበብና ከመደጋገፍ ባሻገር በተናጠልም ይሁን በቡድን ለአንድ ግብ መሥራትን እንደሚፈልግ ያስረዳሉ። በተጨማሪም ይህንን ግብ እውን ለማድረግና የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የቱሪዝም ዘርፍ ማኅበራት ድርሻ ጉልህ እንደሆነ ያነሳሉ።

የሆቴል፣ የቱር ኦፐሬተር፣ አስጎብኚዎች፣ የቱሪዝም ምርት ተሳታፊዎች፣ የትራንስፖርት አቅራቢዎች እና ~~የዘርፉ ልዩ~~ ልዩ ባለሙያዎች ጥምረት የኢትዮጵያን እምቅ የቱሪዝም ሀብት (ጭስ አልባ ኢንዱስትሪ) ወደ ኢኮኖሚ ጉልበት ለመቀየር ትልቅ አቅም እንደሆነ ይነገራል። ይህን መሰል ጥምረት በሀገራችን በስፋት ባይታይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢንዱስትሪውን መነቃቃት ተከትሎ በማኅበር የመሰባሰብ ፍላጎት እየታየ ነው። ለምሳሌ ከሚጠቀሱ የቱሪዝም የሙያ ማኅበራት ውስጥ ደግሞ ባሳለፍነው ሳምንት በይፋ የተመሠረተው የአዲስ አበባ ሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያዎች ማኅበር አንዱ ነው።

የአዲስ አበባ ሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ አሸናፊ ሙሉጌታ ስለማኅበሩ ምስረታና የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባኤው ሲያስረዱ፤ «መሥራች አባላት በኢንዱስትሪው ከፍተኛ ልምድ፣ ብቃት፣ ፍላጎት፣ ልዩ ተነሳሽነትና ለረጅም ዓመታት የአገልግሎት እውቅት ዝግጅት ባላቸው ቀና አባላት የተመሠረተ ነው። በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን መዝገብ ቁጥር 6958 የተመዘገበ የባለሙያዎች ማኅበር ነው» ይላሉ።

ማኅበሩ በአዲስ አበባ የሆቴልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪው የላቀ ደረጃን፣ ትብብርን እና ቀጣይነት ያለው ዕድገትን ለማስተዋወቅ ቀዳሚና ተደማጭነት ያለው ማኅበር የመሆን ራዕይን እንዳስቀመጠም የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ይገልፃሉ። ለከተማዋ ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት እና የነዋሪዎቿን ሕይወት የሚያበለጽግ ዓለም አቀፍ እውቅና ያለው ማኅበር በመሆን የሆቴልና ቱሪዝም ለማሳደግ እንደሚሠሩ ይናገራሉ።

«ልህቀትና ተባባሪነት ማዕረጋችን ነው» የሚሉት ፕሬዚዳንቱ የማኅበሩ ዋና ተልዕኮ የአዲስ አበባን የሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያዎችን ማስተባበር፣ ለአባላቶቻቸው የሥልጠና እንዲሁም የትምህርት ዕድሎች ማቅረብ፣ ጠቃሚ ትስስሮችን (networking) መመሥረትና በሙያዊ ሥነ ምግባር ማብቃት መሆኑን ይገልፃሉ። የአባላትን ሙያዊ ክህሎት እና እውቀት ለማሳደግ፣ የሥነምግባር ልምዶችን ለማስተዋወቅ፣ ፈጠራን እንዲሁም ተወዳዳሪነትን በኢንዱስትሪው ውስጥ ለመምራት በቁርጠኝነት ለመሥራት እንደተነሱም ያስረዳሉ።

«የአዲስ አበባ ሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያዎች ማኅበር የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ከሀገሪቱ አምስት የኢኮኖሚ ምሰሶዎች ውስጥ አንዱ ሆኖ ከመመደቡ ጋር ተያይዞም የፖሊሲ ግብአቶችን ለሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ያቀርባል፣ ያወያያል እንዲሁም በቅርበት ለተፈፃሚነታቸው ይሠራል» የሚሉት የማኅበሩ ፕሬዚዳንት አቶ አሸናፊ ሙሉጌታ፤ አዲስ አበባ ከኒዮርክ እና ከጄኔቫ በመቀጠል ሦስተኛዋ የበርካታ ዲፕሎማቶች መቀመጫ እንደመሆኗ በከተማው የሆቴልና ቱሪዝም አገልግሎት አሰጣጥን በማዘመን ለሀገር ውስጥ እንዲሁም ለዓለም አቀፍ ጎብኚዎች የሚመች እና የሚመጥን ሙያዊ ልህቀት እንዲኖር ከማኅበሩ አባላት ጋር እንደሚሠሩ ገልፀዋል።

«የከተማችንን እና የሀገራችንን ገፅታ በማሳደግ እና



በማህበሩ ምስረታ ላይ የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታውና አቶ ስለሺ ግርማን ጨምሮ የተለያዩ መስሪያቤቶች ኃላፊዎችና አካላት ተገኝተዋል

**የአዲስ አበባ ሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያዎች ለከተማዋና ዘርፉን ለሚመራው ቢሮ በእጅጉ አስፈላጊ ነው። በተለይ ከቱሪዝም ዘርፍ ከተማው ሊሠራና ሊያሳካ ያቀዳቸውን ተግባራት ስኬታማ ለማድረግ ማኅበሩ አጋዥ ኃይል ነው**

ለሌሎች የቱሪስት መዳረሻዎች ምቹ ሁኔታን የምንፈጥር ይሆናል» የሚሉት ፕሬዚዳንቱ ማኅበሩ በዘርፉ በጥናትና ምርምር፣ በሥልጠናና በማማከር ሙያዊ አበርክቶን ለመወጣት እቅድ ይዞ የተነሳ መሆኑን ይናገራሉ። ከዚህም ባሻገር በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሙያዎች ምቹ የሥራ ሁኔታ እንደሚፈጥሩ ይገልፃሉ። ይህንን ርዕይ ለማሳካትም ከሚመለከታቸው የመንግሥት እና የግል ተቋማት ጋር በቅርበት እንደሚሠሩ ያስረዳሉ። የቱሪዝም ዘርፍ በትብብር እና ቅንጅት መሥራትን እንደሚፈልግ የሚገልፁት የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ይህንን አስመልክቶ ከመንግሥት ተቋማት፣ ኤጀንሲዎች፣ ከኢንዱስትሪ ባለድርሻ አካላት እና ፖሊሲ አውጪዎች ጋር በንቃት በመሳተፍ የዘርፉን እድገትና ልማት የሚደግፉ ፖሊሲዎችና ደንቦች ለመቅረጽ እንደሚሰሩ ይናገራሉ። ለዘላቂ የቱሪዝም ልምዶች የመሠረተ ልማት ማሻሻያዎች እና የከተማዋን እንደ መዳረሻ መስህብ የሚያጎለብቱ ጅምር ሥራዎችን ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው አጋዥ ኃይል እንደሚሆኑም ነው የተናገሩት።

በምስረታው ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሳው እንደሚናገሩት፤ የአዲስ አበባ ሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያዎች ለከተማዋና ዘርፉን ለሚመራው ቢሮ በእጅጉ አስፈላጊ ነው። በተለይ ከቱሪዝም ዘርፍ ከተማው ሊሠራና ሊያሳካ ያቀዳቸውን ተግባራት ስኬታማ ለማድረግ ማኅበሩ አጋዥ ኃይል ነው። አባላቱ ረዘም ያሉ ዓመታት በዘርፉ ልምድ ያካበቱና በቂ እውቀት ያላቸው በመሆኑ የከተማዋን የቱሪዝም እድገት ለማፋጠን ከማገዝም ባሻገር ለሀገር እና ለመላው አፍሪካ ተጨማሪ አቅም ይሆናሉ። በተለይ ከሥነ ምግባር እና ዘርፉ የሚፈልገውን ሙያዊ አገልግሎት ከማቅረብ አንፃር በማኅበሩ የተሰባሰቡት ባለሙያዎች የሚኖራቸው አበርክቶና ድርሻ ከፍተኛ ነው።

«በቱሪዝም ዘርፍ ላይ ያሉ ማኅበራት ድንበር የላቸውም» የሚሉት የቢሮ ኃላፊዋ፤ የሚታዩ ክፍተቶች፣ መሻሻል የሚገባቸው ነገሮችን ጨምሮ ዘርፉን ለማሳደግ የሚጠቅሙ ምክረ ሃሳቦችን የሆስፒታሊቲና አገልግሎት ዘርፍ እውቀቶችን መለዋወጥ እንደሚገባ ይናገራሉ። ምስረታውን ይፋ ያደረገው ማኅበርም ይህንኑ ሚናውን እንደሚወጣ እምነታቸው እንደሆነ ይናገራሉ። አዲስ አበባ በቱሪዝም ሀብትነት የሚገለፁ ሁሉንም ገፀ በረከቶች የያዘች መሆኗን በማንሳትም እነዚህን ፀጋዎች ተረድቶና አልምቶ ለሀገር ኢኮኖሚ እድገትና ገፅታ ግንባታ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል። ከዚህ አንፃር ማኅበሩ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ጥሪ አቅርበዋል።

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ እንደሚሉት፣ ባለፉት ጊዜያት በቱሪዝም ዘርፍ የደረሱ ጉዳቶችና ጫናዎችን በመቋቋም አሁንም ድረስ ተስፋ ሰንቀው ለኢንዱስትሪው እድገት የሚሠሩ አሉ። በተለይ በቱሪዝም ዘርፍ በትብብርና በቅንጅት መሥራት አስፈላጊ መሆኑን በማመን የአዲስ አበባ ሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያዎች ማኅበርን መመሥረት ተጨማሪ አቅም ይሆናል። በቱሪዝም ዘርፍ ላይ ቆየት ያሉ ነባር ማኅበራት፣ ባለሙያዎች እንዲሁም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መደጋገፍና አብሮ መሥራት ቱሪዝም ሚኒስቴር እራሱን ችሎ እንዲቋቋምና ከአምስቱ የኢኮኖሚ ምሰሶዎች መካከል አንዱ እንዲሆን የራሱን ድርሻ ተወጥቷል።

«ለቱሪዝም እድገት የግሉ ዘርፍና የሲቪክ ሶሳይቲ ተዋንያን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው» ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በተለይ ዘላቂ የቱሪዝም ልማት ለማምጣት በቀዳሚነት የግሉ ዘርፍ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ይናገራሉ። የአዲስ አበባ የሆቴል ቱሪዝም ባለሙያዎች ማኅበር ከእነዚህ ውስጥ አንዱ መሆኑን ገልፀው ይህንን መሰል ማኅበራት መፈጠራቸው በዘርፉ ለማምጣት ለሚፈለገው ስር ነቀል ለውጥ ጉልበት እንደሚሆኑ ይገልፃሉ። በተለይ ማኅበራት ለቱሪዝም ዘርፉ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦን በተመለከተ የነበረውን ሰፊ ክፍተት የሚሞላና ፋይዳውም ከፍተኛ እንደሆነ ይናገራሉ።

የቱሪዝም የጥናትና ምርምር ሥራዎች ላይ የሚሳተፈውና በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ውስጥ በመምህርነት የሚያገለግለው አቶ በቀለ ኡማ በበኩሉ የማኅበሩ ምሥረታና ይዞት የመጣውን የትግበራ ሂደት አስመልክቶ አጭር ዳሰሳዊ ጽሑፍ አቅርቧል። በማብራሪያውም ቱሪዝም ከሌሎች ዘርፎች በተሻለ ከፍተኛ የሰው ኃይል የመያዝና የሥራ ዕድል የመፍጠር አቅም እንዳለው ይናገራል። ይህንን ዘርፍ በብቃት ለመምራትና የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ከመንግሥት ባሻገር የግሉ ዘርፍና ሲቪክ ሶሳይቲዎች በቅንጅት መሥራት እንዳለባቸው ይገልፃል። በተለይ በዘርፉ ምስረታውን ይፋ ያደረገው የአዲስ አበባ ሆቴል ቱሪዝም ባለሙያዎች ዓይነት ማኅበራት ጠቀሜታቸው ጉልህ መሆኑን ያነሳል። በዘርፉ ረዘም ላሉ ዓመታት ልምድ ባካበቱ ባለሙያዎች የተመሠረተው የአዲስ አበባ ሆቴል ቱሪዝም ባለሙያዎች ማኅበርም በአዲስ አበባ ከተማና ከፍ ሲል በሀገር ደረጃ የኢትዮጵያ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ እንዲያድግ የድርሻውን የሚወጣ እንደሆነ ይገልፃል።

«የሆስፒታሊቲና ቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ ተወዳዳሪነትን የሚጠይቅና ቀጣይነት ያለው ተከታታይ ለውጦችን የሚሻ ነው» የሚለው አቶ በቀለ ኡማ፤ ይህንን እውን ለማድረግ በዘርፉ ያሉ የሆቴል፣ የአገልግሎት ዘርፍ ተቋማት፣ አስጎብኚዎች፣ ቱር ኦፐሬተርስና መሰል ባለሙያዎች በጥምረት ቢሠሩ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚችሉ ይናገራል። ለዚህም ጠንካራ ማኅበራት ወሳኝ ድርሻ እንደሚይዙ ይገልፃል። በተለይ በግሉ ዘርፍ አቅም የማይሞከሩ የመሠረተ ልማቶች እና የመዳረሻ ልማት ሥራዎች ላይ መንግሥት ኃላፊነቱን ወስዶ ሥራዎችን ሲሠራ ማኅበራቶች በማማከር ሙያዊ ድጋፍ መስጠት፣ ጥናትና ምርምር ላይ ለመሳተፍ፣ የፖሊሲና ሕጎች ላይ ግብአት በማቅረብ ረገድ የድርሻቸውን መወጣት እንደሚችሉ ይገልፃል። አዲስ አበባን መሠረት አድርጎ የተመሠረተው ማኅበርም ይህንኑ ኃላፊነት እንደ አንድ የሙያ ግዴታው በመቁጠር ኃላፊነት እንደሚወስድ ይናገራል።

«የአዲስ አበባ የሆቴል ቱሪዝም ባለሙያዎች በቱሪዝም ዘርፍ ውስጥ ያሉ ንግዶች ራሳቸውን ችለው በጥንካሬ ቆመው መንግሥትን ለመደገፍ እንዲችሉ ያመቻቻል» የሚለው አቶ በቀለ ኡማ፤ በዘርፉ ያሉ ንግዶች እራሳቸውን ከቻሉ መንግሥት ከግብርና ልዩ ልዩ ጥቅሞች በሚያገኘው የኢኮኖሚ ድጋፍ መሠረተ ልማቶችን ለመደገፍ እንደሚያስችለው ይገልፃል። ማኅበረሰቡም የሥራ ዕድል እንዲያገኝ እና እራሱን እንዲለውጥ ከማድረግ አንፃርም የበኩሉን እንደሚወጣ ይናገራሉ።

አዲስ አበባ ከተማ ከኒዮርክና ጄኔቫ ቀጥላ በርካታ ዓለም አቀፍ ተቋማት የሚገኙበት በመሆኗ ምክንያት በተለይ በሆስፒታሊቲና ቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ የማደግ ዕድል እንዳላት የሚገልፀው መምህሩና የጥናትና ምርምር ምሁሩ በቀለ ኡማ፣ የአዲስ አበባ ሆቴልና ቱሪዝም ባለሙያዎች ማኅበር ይህንን ዕድል ተጠቅሞ ኢትዮጵያ ከቱሪዝሙ ዘርፍ ተጠቃሚ እንድትሆን የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በማቅረብ፣ የቱሪስት ፍሰቱን የሚጨምር ስልት በመንደፍና ለመንግሥት በማቅረብ፣ የተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች በኢትዮጵያ እንዲካሄዱና የማይስ ቱሪዝም እንዲበረታታ ለማስቻል ውትወታ (Advocacy) በመሥራት እንደሚሳተፍ እና የዘርፉ አጋዥ ኃይል እንደሚሆን አስረድቷል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በዓለም ታሪክ

**ዋለልኝ አየለ**

የዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ክስተቶች ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮችን ያስታውሱናል። ወደ ዋናው የዓለም ጦርነት ታሪክ ከመሄዳችን በፊት መጀመሪያ በዚህ ሳምንት የተከሰቱ የሀገራችን ታሪኮችን እና ሌሎች የዓለም ክስተቶችን በአጭሩ እናስታውስ።

ከ92 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ነሐሴ 23 ቀን 1923 ዓ.ም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በግርማዊ ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በ750 ሺህ ፓውንድ መነሻ ሀብት ተቋቋመ።

በዚሁ ሳምንት ከ158 ዓመታት በፊት ነሐሴ 24 ቀን 1857 ዓ.ም ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ ሆኑ፤ ‹‹ምኒልክ ንጉሠ ሸዋ›› ተብለው ነገሡ።

ከ60 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ነሐሴ 22 ቀን 1955 ዓ.ም አሜሪካዊው የመብት ተሟጋች ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር ‹‹ህልም አለኝ›› የሚለውን ዓለም አቀፋዊ ዝና ያተረፈውን ታሪካዊ ንግግር አደረገ። ‹‹March on Washington for Jobs and Freedom›› በተባለው ትዕይንተ ሕዝብ ላይ የቀረበውን ይህን ንግግር፣ ከ250 ሺህ በላይ የሚሆኑ የእኩልነት መብት ደጋፊዎችና አቀንቃኞች ዋሺንግተን ዲ.ሲ በሚገኘው የሊንከን መታሰቢያ አደባባይ ተገኝተው ተከታትለውታል። ዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር የሲቪልና የኢኮኖሚ መብቶች እንዲከበሩና የዘር መድሎና መገለል እንዲቆም ጥሪ ያቀረቡበት ይህ ታሪካዊ ንግግራቸው፣ ዛሬም ጭቆናና መገፋት ያንገሸገሻቸው የዓለም ሕዝቦች እንደስንቅና የትግል መዝሙራቸው ይጠቀሙበታል። ‹‹ህልም አለኝ›› የሚለው ንግግርም በብዙ ቦታዎችና አጋጣሚዎች ይነገራል።

ከ84 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ነሐሴ 26 ቀን 1931 ዓ.ም (በአውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር መስከረም 1 ቀን 1939) የአዶልፍ ሂትለር የናዚ ሠራዊት ፖላንድን ከወረረ በኋላ፤ ብሪታንያ እና ፈረንሳይ ተጣምረው ጀርመን ላይ ጦርነት አወጁ። ይህም ጦርነት የሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጀመርን አረጋገጠ። ይህ ጦርነት ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ይባላል። በዛሬው ሳምንቱ በታሪክ ዓምዳችን ሁለተኛውን የዓለም ጦርነት እናስታውሳለን።

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ብዙ ዓለም አቀፍ ገጽታዎችን ቀይሯል፤ ብዙ ተቋማትና የሀገራት ጥምረቶች እንዲፈጠሩ አድርጓል። በብዙ ታሪኮች ውስጥ ስሙ ይነሳል። በተለይም የአውሮፓ ሀገራት ታሪክ፣ የተቋማትና ማህበራት ታሪካዊ ዳራ የሚገለጸው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጋር በተያያዘ ነው። በአጠቃላይ የዓለምን ገጽታ የቀየረ ጦርነት ነው። የዓለም ጦርነት የተባለውም ለዚህ ነው።

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጀመር ምክንያቶች ብዙ ቢሆኑም መነሻ ሰበቧ ግን የጀርመን ፖላንድ ላይ ጥቃት መሰንዘር ነው። ፖላንድ ላይ ጥቃት ሲሰነዘር ከፖላንድ ጋር ስምምነት ያደረገችው ታላቋ ብሪታንያ እና ፈረንሳይ ከሁለት ቀን በኋላ ነሐሴ 28 ቀን 1931 ዓ.ም (በአውሮፓውያኑ መስከረም 3 ቀን 1939 ማለት ነው) ጀርመን ላይ ጦርነት አወጁ። ይሁን እንጂ እነዚህ ሀገሮች ፖላንድን ለመርዳት ወታደሮች እና መሣሪያዎችን በፍጥነት ማሰባሰብ አልቻሉም፤ ጀርመን በምዕራባዊው ፖላንድ ድል ከተሳካ በኋላ ሶቪየቶች ከጀርመን ጋር ባደረጉት ስምምነት መሠረት ከአውሮፓውያኑ መስከረም 17 ጀምሮ ፖላንድን ማዳከም ጀመሩ። በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር መስከረም 27 ቀን 1939 ፖላንድ እጅ ሰጠች። ሆኖም ጦርነቱ የተጠናቀቀው በጦርነቱ ለኳሽ በናዚ ጀርመን ሽንፈት፤ በተባበሩት ተጓዳኝ ኃይሎች ማለትም በአሜሪካን በብሪታኒያ በፈረንሳይ እና በሶቭየት ኅብረት ድል አድራጊት ነው።

የተጓዳኝ መንግሥታት (Allied powers) ከፍተኛ ወታደራዊ ባለሥልጣናት በተገኙበት የናዚ ጀርመን የተለያዩ ክፍለ ጦሮች የበላይ አዛዦች በተዘጋጀ ሰነድ ላይ ጀርመን ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ እጅ መስጠቷን በርሊን ከተማ በሀገሩ ሰዓት አቆጣጠር ለእኩለ ሌሊት 15 ደቂቃ ሲቀረው በፊርማቸው አረጋገጡ። ይህም ጀነራል አልፍሬድ ዮሴፍ ፈርዲናድ ዮድል በተባለ የጀርመን የመከላከያ ኃይል ከፍተኛ የጦር አዛዥ በራድዮ ተነገረ። ‹‹እኛ ከዚህ በታች ፊርማችንን ያስቀመጥን የጦር አዛዦች ያለ አንዳች ቅድመ ግዴታ ሀገሪቱ እጅ መስጠቷን እናረጋግጣለን። ስለሆነም በምድር በባህር እና በአየር የተሰማሩ እስካሁን በጀርመናውያን የሚታዘዙ ኃይሎቻችንን በሙሉ በሶቭየት ቀዩ ጦር የበላይ አመራር ስር መሆናቸውን እናረጋግጣለን››



የጀርመንን ሽንፈት በፊርማቸው ያረጋገጡት፤ የናዚ ጀርመን የጦር ኃይሎች ዋና አዛዥ ፊልድ ማርሻል ቪልሄልም ካይትል፣ የአየር ኃይሉ አዛዥ ሃንስ ዩርገን ሃንስ ሽቱምፕፍ ና የባህር ኃይሉ አዛዥ አድሚራል ሃንስ ጌዮርግ ፎን ፍሪድቡርግ ናቸው። የሙኒኩ የታሪክ ተቋም ባልደረባ የታሪክ ምሁሩ ዮሐንስ ሁርተር ያኔ የሆነውን ‹‹ጀርመን እጅ መስጠቷን ያረጋገጠው የያኔው የጀርመን መንግሥት ሳይሆን የጦር ኃይሉ ነው። በሕጋዊ አመለካከት ይህ በእነዚያ ቀናት ከተፈፀሙት አስገራሚ ነገሮች አንዱ ነው›› ይሉታል።

ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት መነሻ የጀርመን ፖላንድን ማጥቃት እንደ ቅጽበታዊ ሰበብ ቢቆጠርም ጀርመን ይህን ለማድረጓ ደግሞ የሚዘረዘሩ ሌሎች ምክንያቶች አሉ። በአንደኛው የዓለም ጦርነት ፖላንድ በለስ ቀንቷት ጀርመንን ለሁለት ከፍላ የባህር በር ባለቤት ሆነች። ይህ ደግሞ ጀርመንን አስከፍቶ አለፈ። ጀርመን ፖላንድን ለማጥቃቷ አንድ ትልቅ ምክንያት ተወለደ ማለት ነው። ይህ እና ሌሎች ምክንያቶች በአጠቃላይ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ምክንያቶች ተብለው ይጠቀሳሉ። ጀርመን ፖላንድን ለማጥቃቷም ሆነ ለአጠቃላይ መጀመሩ ምክንያት ናቸው የተባሉትን እንጠቃቅስ።

አንደኛው ምክንያት ቬርሳይል ስምምነት የሚባለው ነው። በዚህ ስምምነት በአንደኛው የዓለም ጦርነት አሸናፊ የነበሩት ተጓዳኝ ኃይሎች (ፈረንሳይ፣ ታላቋ ብሪታንያ፣ ሩሲያ፣ ጣሊያን፣ ጃፓን፣ አሜሪካ) በጀርመን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ላይ ወሰኑ። ጀርመን ይህን የቬርሳይል ስምምነት እንድትፈርም ተገደደች። በስምምነቱም ጥፋተኝነቷን አምና ካሳ እንድትከፍል ተደረገች። ግዙፍ ወታደራዊ አቅም እንዳትገነባም እገዳዎች ተደረጉባት።

ሌላው ምክንያት የሚባለው በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ምክንያት የኢኮኖሚ መዳከም ነው። ንግድ ቀነሰ፣ የቢዝነስ ሥራዎች ተዘጉ፣ባንኮች ተራቆቱ፣ ሥራ አጥነት ተስፋፋ፤ በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ተቃወሰ። በዚህን ጊዜ ሕዝቡ ጠንካራ መሪ መመኘት ጀመረ፤ ይህኔ ነው የወቅቱ የጀርመን መሪ አዶልፍ ሂትለር እነዚህን ሁሉ ችግሮች እንደሚቀርፍና ጠንካራ መንግሥት እንደሚሆን ለጀርመን መንግሥት ቃል የገባው።

ከዚህ በኋላ እንደ ምክንያት የተጠቀሰው እንግዲህ የጀርመን በጦር አቅም መደርጀት ነው። በቬርሳይል ስምምነት ግዙፍ የጦር አቅም እንዳይኖረው እገዳ ቢደረግበትም፤ ሂትለር በምሥጢር የጦር አቅሙን ማጎልበት ጀመረ። ምንም እንኳን ፈረንሳይ እና እንግሊዝ የሂትለርን የጦር ዝግጅት ቢያውቁም፤ ዳሩ ግን የጀርመን መጠናከር ከሩሲያ የሚመጣውን የኮሚኒዝም መስፋፋት ያስቆምልናል በሚል ባላየ አልፈውታል።

በአውሮፓውያኑ 1936 ሂትለር የጀርመን ወታደሮችን ጀርመንኛ በሚናገሩ የፈረንሳይ አካባቢዎች አሰማርቷል። ወደ አስትሪያና ችኮስሎቫኪያም አሰማርቷል። በዚህን ጊዜ እንግሊዝም ሆነች ፈረንሳይ የጦር ዝግጅት አላደረጉም ነበር። በዚሁ ዓመት ሂትለር ከጣሊያን እና ጃፓን ጋር አጋርነት (alliances) ፈጠረ። ይህ የጀርመን፣ ጣሊያን እና ጃፓን የጦር ጥምረት አክሲስ (Axis) ይባል ነበር።

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተጀመረበት ሌላኛው ምክንያት ግጭትን የማስቀረት ስምምነት (Appeasement) አለመሳካቱ ነው። በአውሮፓውያኑ 1930ዎቹ መጀመሪያ የተደረገው የቬርሳይል ስምምነት ጀርመንን የበደለ እንደነበር የእንግሊዝና የፈረንሳይ ፖለቲከኞች አመኑ። ስለዚህ የሂትለር እርምጃ የሚጠበቅና ፍትሐዊ ነበር ተብሎ ታመነ። ይህን በማመናቸውም ሌላ ስምምነት ተደረገ። ይህም በአውሮፓውያኑ 1938 የተደረገው የሙኒክ ስምምነት ነው። በዚህ በሙኒክ ስምምነት ጀርመን ቼኮዝሎቫኪያ ውስጥ ጀርመንኛ ተናጋሪዎች ያሉበትን መሬት እንድትወስድ እንግሊዝና ፈረንሳይ ፈቀዱ። ጀርመንም የተቀረውን የቼኮዝሎቫኪያ ክፍልም ሆነ ሌላ ሀገር ላትወር ተስማማች። ሆኖም ግን በአውሮፓውያኑ መጋቢት 1938 ጀርመን ስምምነቷን አፍርሳ የተቀረውን የቼኮዝሎቫኪያ ክፍል ወረረች። ጀርመን ይህን ስታደርግ እንግሊዝም ሆነች ፈረንሳይ ወታደራዊ እርምጃ ለመውሰድ አልተዘጋጁም ነበር። ከዚያም በአውሮፓውያኑ መስከረም 1 ቀን 1938 ጀርመን ፖላንድን ወረረች። እንግሊዝና ፈረንሳይም ወዲያውኑ በጀርመን ላይ ጦርነት አዋጁ። ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በአውሮፓ ተጀመረ ማለት ነው።

ይህ ሁሉ ሲሆን የመንግሥታቱ ማኅበር (League of Nations) ጦርነቱን ማስቀረት አልቻለም ነበር፤ ሁለተኛውን የዓለም ጦርነት ክስተቶች የሚያብራሩ ሰነዶች የማኅበሩን ክሽፈት እንደ አንድ ምክንያት ይጠቅሱታል። በአውሮፓውያኑ የቀመር ቀመር ጥር 10 ቀን 1920 የተቋቋመው የመንግሥታቱ ማኅበር የተቋቋመበት ዋና ዓላማ የዓለምን ሰላም ማስጠበቅ ነበር። ሁሉንም ሀገራት አባል አድርጎ፤ በሀገራት መካከል አለመግባባት ሲፈጠር በድርድርና ውይይት ማስፈታት ነበር ዓላማው፤ ዳሩ ግን በታሰበለት ዓላማ አልሠራም። ሁሉንም የዓለም ሀገራት አባል ማድረግም አልቻለም። አባል ለሆኑትም ፍትሕ ሊጠይቅ አልቻለም፤ ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት ፊቱን ማዞሩ አንዱ ማሳያ ነው። ጃፓን ቻይናን በወረረችበት ጊዜም ተመሳሳይ አድሎ ፈጽሟል።

የጃፓን ቻይናን፣ ቬትናምን እና ሌሎች እስያ ውስጥ የሚገኙ ግዛቶችን መውረሯ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት አካል ተደርጎ ይወሰዳል። በአውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር በ1931 ጀርመን በከፍተኛ የኢኮኖሚ ድቀት ተመታች። የጃፓን ሕዝብ በመንግሥት እምነት አጣ። ለገጠማቸው ኢኮኖሚያዊ ችግር መፍትሔው ወታደራዊ አቅምን ማፈርጠም ሳይሆን አይቀርም ብለው አሰቡ። ምርቶችን ለማምረት ጥሬ ሀብት እንደሚያስፈልግ አመኑ። ይህን ማግኘት የሚቻለው ደግሞ ጥሬ ሀብት ያላቸውን አካባቢዎች በመውረር ነው። ጃፓን እንደ ማዕድን ያሉ ጥሬ ሀብቶች ያሉባቸውን የቻይና አካባቢዎች ወረረች። ቻይና ለመንግሥታቱ ማህበር ‹‹አቤት›› ብትልም የመንግሥታቱ ማኅበር አሁንም የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ እንዳለ ነው። ጃፓን በወረራዋ ቀጥላ ወደ ኮሪያ ሁሉ ተጓዘች። እንዲህ እንዲህ እያለ የቀጠለው የጃፓን እንቅስቃሴ ደግሞ በአውሮፓውያኑ ታኅሣሥ 1941 ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በእስያ እንዲጀመር አድርጓል።

በዚህ አስከፊ ጦርነት ከዛሬ 84 ዓመታት በፊት ዓለም ከ70 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ አጥታለች። ያኔ የነበረው የየሀገራቱ የሕዝብ ቁጥር እንደዛሬው አይደለም። በዚያን ዘመን ይህን ያህል ሚሊዮን ሕዝብ ማጣት የዓለምን ነባራዊ ሁኔታ ይቀይራል። እስከ አሁን ባለው የጦርነት ታሪክም በአስከፊነቱ የሚጠቀሰው ይህ ጦርነት ነው።

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ምክንያቶች አንዱ የአንደኛው የዓለም ጦርነት ጣጣዎች ናቸው። ከዚህ የምንረዳው አንድ ጦርነት ለሌላ ጦርነት ምክንያት እንደሚሆን ነው። ደግነቱ የአውሮፓ ሀገራት ዛሬ ሰልጥነዋል። የዓለም የጦርነት አስጀማሪና የጦርነት ምሳሌ እንዳልነበሩ፣ ዛሬ ግን በሀገራት መካከል ወታደራዊ ድንበር ጠባቂ የላቸውም እስከሚባልላቸው ድረስ ሰልጥነዋል። የሀገራቸው መገናኛ ብዙኃን የ24 ሰዓት የጦርነት ዜናዎቻቸው የአፍሪካና የሌሎች አህጉራት ጦርነቶች ናቸው። አንደኛውንም ሆነ ሁለተኛውን የዓለም ጦርነቶች የሚያስታውሷቸው በታሪክነታቸው ብቻ ነው።

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እነሆ በተለያዩ አጋጣሚዎች በታሪክነቱ ይታወሳል፤ የጦርነትን አስከፊነትም ሲናገር ይኖራል!

# የዝነኞች ገጽ

# እንቁጣጣሽ አብሳሪው ድምፃዊ

ቤዛ እሸቱ

የነሐሴ ጭጋግ በርግጥ ሊለቅ ስለመሆኑ ማረጋገጫው በሀገራችን የሚገኙ አብዛኞቹ የቴሌቪዥንና የሬድዮ ጣቢያዎች መተኪያ ያላገኙለትን አንድ ዜማ በተደጋጋሚ ለአየር ማብቃታቸው ነው። «ስርቅታዬ» የተሰኘው ዘፈን በመገናኛ ብዙኃኑ፤ እንዲሁም በብዙኃኑ አድማጭ ቤት መሰማቱ ለቡሄ መድረስና ለአዲስ ዓመት መቃረብ አብሳሪ ነው። ዘፈኑን በቴሌቪዥን ያኔም ሆነ አሁን ያዩትና የሚያዩት ነጭ የባህል ልብስ ከቢጫ ጥለት ጋር ያደረገ፤ እራሱም አዲስ ዓመት የመሰለ ወጣት ከዘፈኑ እኩል የብዙዎች ትውስታ ሆኗል።

በቄለም ወለጋ፣ ደንቢ ዶሎ የተወለደው ድምጻዊ ሰለሞን ደነቀ ታላቅ እህቱን ተከትሎ ለቤተሰቡ ሁለተኛ ልጅ በመሆን በ1951 ዓ.ም ይህችን ዓለም ተቀላቀለ። ሰለሞን ከአብዛኛው ኢትዮጵያዊ የተለየ አስተዳደግ ነበረው። ይኸውም በርካቶች ጥበብን ለመቀላቀል ሲፍጨረጨሩ ኮርኳሚ የሚበዛበት ሕይወት ቢያሳልፉም እሱ ግን ሙዚቃን ለመሞከር ሲጥር አዲስ የሙዚቃ መሣሪያ የመግዛት አቅም ባይኖራቸውም፣ ወላጅ እናቱ በአካባቢው ካገኙት መሣሪያ ክራር ሠርተው ተሰጥኦውን እንዲያዳብር ያደርጉት ነበር።

ያችን ክራር ይዞ ጊቢያቸው ውስጥ ከሚገኝ ዛፍ ላይ ረዥም ጊዜውን ያሳልፍ እንደነበር ታላቅ እህቱ ታደለች ደነቀ ታስታውሳለች። ከትምህርትና ሙዚቃን በግል ከመዝፈን በተረፈ ሰለሞን በልጅነት ጊዜው ከቤተክርስቲያን የማይጠፋ ነበር። ድምጹ በያሬዳዊ ዜማ መቃኘቱ ሰለሞን ለሚታወቅበት ስርቅርቅ ድምጽ አስተዋጽኦው የጎላ እንደሆነ ይታመናል። ከተወለደበት የደንቢ ዶሎ ከተማ የሙዚቃ ሥራውን ለማሳደግ ወደ ነቀምት አመራ። በነቀምት ጉደቱ ወለጋ የኪነጥበብ ቡድንን ተቀላቀለ።

የኪነት ቡድኑን የተቀላቀለው በመሣሪያ ተጫዋችነት ነበር። ከልጅነቱ ክራር ይጫወት ነበርና እሱን ቡድኑ አዳበረለት። በሂደት ጊታር መጫወትን አከለበት። ምንም እንኳን የሙዚቃ ትምህርት ቤት ገብቶ ባይማርም መሰንቆ፣ አኮርዲዮን፣ ትራምፔት መጫወት ይችላል። ሁለገብ ዜማ ይደርሳል፤ ግጥም ይጽፋል። በዚሁ ችሎታውም አብረውት የሠሩት ለመድረክ የተፈጠረ ነው ይሉታል። የድምጹማ ነገር ምን ይጠየቃል፤ በርካቶች ድምጹ ስርቅርቅ መሆኑን ተስማምተውበታል። በኪነት ቡድኑ በርካታ ሥራዎችን ከሠራ በኋላ የመጀመሪያ የአልበም ሥራውን ለማውጣት ወደ አዲስ አበባ አመራ። አዲስ አበባ ከደረሰ በኋላም በበርካታ የሀገሪቱ ትልልቅ መድረኮች ላይ በግሩም ድምጹ አቀንቅኗል። ከአምስት በላይ አልበሞችንም ለአድማጩ አድርሷል።

በርካታ ዘፈኖች ቢኖሩትም የሰለሞን የተለየ መለያው፣ መታወቂያና መታወሻው ግን ስርቅታዬ የተሰኘ ዘፈኑ ነው። ስርቅታ የፍቅር፣ የቡሄ፣ የእንቁጣጣሽ፣ የትዝታ የባህል ዘፈን ሆኖ ሰባት ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የሀገራችንን አኗኗር፣ የበዓል አውድን፤ ብሎም የልጅነት ትውስታን ማሳየት የቻለ ድንቅ ድምጻዊ ነው።

በዚያች ዘመን አይሸሬ ውብ ዜማ በስቅታ የተቸገረው ሰለሞን ማን እንዳነሳው ለማወቅ ይቸገራል።

ማን አነሳኝ ደግሞ ትዝታ
ትሁን ቆንጆት ነች ስመኝሽ

እያለ ዘፈኑ ሲጀምር የበዓል ልብስ ከመልበሱ በስተቀር ዘፈኑ ወደ መነፋፈቅ ያደላ የፍቅር ዘፈን ይመስላል። አድማጩ የፍቅር ዘፈን ብቻ ቢመስለውም አይፈረድበትም። ሰለሞንና ምናቡ የፈጠራት ስመኝሽ ብዙ የልጅነት ትዝታ ያላቸው ሲሆን፤ እሱም በዘፈኑ ይገለጻል። በስቅታው መነሻነት የትምህርት ቤት ቆይታቸውንና የልጅነት ምኞቱን ተናግሮ ሲያበቃ በአዲስ ዓመት ሲገናኙ የነበረውን ስሜት እንዲህ ሲል ያስታውሰናል።

ከነማስረጃው ስሚ ትዝታ
ትምህርት ቤት ተገብቶ አሀሀሀ
ሁሉም እረፍት ጨርሶ እህህ
ለእንቁጣጣሽ ዝግጅት አሀሀሀ
ቅዱስ ዮሐንስ ደርሶ
ሁሉም ብቅ ብቅ ሲል አሀሀሀ
አዳዲስ ልብስ ለብሶ
ሎሚና እንግጫ እህ
ተይዞ አበባ በዘመድ አዝማድ እህ
ደጃፍ ሲገባ እህ
ሁሉም ሲጋበዝ ጠላና ድፎ
የምግብ ዓይነት ሞልቶ ተትረፍርፎ



ድምጻዊ ሰለሞን ደነቀ

ኩታውን አባባ ለብሰው
ጌጡን እማማ
ቤቱ ተጎዝጉዞ በለምለም ቄጤማ

የሰለሞን ስርቅታዬ ሁሉንም የኑሮ ደረጃ በዓል አክባሪ ያማከለ መሆኑ ከሌሎች የበዓል ዘፈኖች ልዩ ያደርገዋል። እሱ የመረጠው ሁሉም ጋ ሊገኝ የሚችለውን ቄጤማ፣ ሎሚ፣ እንግጫ፣ ድፎና ጠላን አጉልቶ ሌሎቹ አንዱ ጋ ተገኝተው አንዱ ጋ ላይገኙ የሚችሉ የምግብና የመጠጥ ዓይነቶችን እያነሳ እንቁልልጭ ከማለት ይልቅ የምግብ ዓይነት «ሞልቶ ተትረፍርፎ . . .» በማለት በጥቅሉ መጥራትን ምርጫው አድርጓል። እሱ የሚጠራቸው ነገሮች የሁሉም ስለሆኑ በሀብታሙም ሆነ በደሃው ዘንድ የበዓል ትዝታና ስሜትን እንደቀሰቀሱ እስካሁን አሉ።

በማኅበረሰባችን የሴትና የወንድ ተብለው የተለዩ የባህል ጨዋታዎች አሉ። እሱ እነዚህን የጨዋታ ሕጎች ማክበርን መርጧል። ዘፈኑ የበዓል ትዝታ እንደመሆኑ በተለምዶ «አበባየሆሽ» በሴቶች የሚጨፈር ነውና እሱ ከማለት ይልቅ በዘዴ በስቅታው እንዳነሳችው የጠረጠራት ስመኝሽ እራሷ እንድትዘፍንልን አድርጓል።

ታስነኪው ነበረ እንዲህ በሚል ዜማ
ሴቷ የምናውቀውን አበባየሆሽ ዜማ ታዜማለች።
አበባየሆሽ ለምለም (2 ጊዜ)
ባልንጀሮቼ ለምለም
ግቡ በተራ ለምለም
እንጨት ሰብሬ ለምለም........

አበባየሆሽ በሀገራችን የእንቁጣጣሽ ዕለት የሚከበር በዓል እንደመሆኑ የእንቁጣጣሽ ቀን ሰለሞንን መስማት አይደንቅ ይሆናል። ግን ዘፈኑን ለቡሄም ተመራጭ ያስደረገው እሱ ወንዶች ለቡሄ የሚጨፍሩትን ሆያ ሆዬ እንዴት ይጨፍር እንደነበረ በስርቅታው አስታኮ ስለሚያስታውሰን ነው።

ቀሰቀሰኝ እ ቀሰቀሰኝ እ ስርቅታዬ
የልጅነት ጨዋታሽ
ከታወሰሽ ከደጃፍሽ
ጎላ አርጌ ሆዬ ስልሽ ሆዬ ስልሽ
ሆያ ሆዬ ሆ
ሆያ ሆዬ ሆ
እዛ ማዶ ሆ ጭስ ይጨሳል ሆ
አጋፋሪ ሆ ይደግሳል ሆ
ያችን ድግስ ሆ ውጩ ውጩ ሆ
ከድንክ አልጋ ሆ ተገልብጬ ሆ
እያለ ይቀጥላል።

ዘፈኑን በቃ ቀለል ብሎ ከጓደኛ ጋር ትዝ አይልህም ትዝ አይልሽም በሚሉት ዓይነት ስሜት የቀረበ መሆኑ ዘፈኑ ላይ የተዳሰሱት ሀሳቦች በሙሉ እንዲታወሱ አድርጓል። ምንም እንኳን ዘፈን ማጠር አለበት ቢባልም፣ ከጥድፊያ ተነስቶ ለወንድ የሰጠውን ክብርና ሙገሳ ለሴት ሳይሰጥ ማቆምን አይመርጥም። «ስርቅታዬ» ምንም እንከን የሌለውና እስካሁን መተኪያ ያልተገኘለት የበዓል ዘፈን ሆኖ ዘልቋል።

ሰለሞንን መድረክ ላይ ሲዘፍን ያዩት በአንድ ነገር ይስማማሉ፤ ሲዘፍን እራሱ ተዝናንቶ ስለሆነ መዝናናቱ እነሱም ላይ ይጋባል። የተለየ የሚያበራ ፈገግታ ነበረው፤ ደግሞም የሚዘፍነውን ስሜት መግለጽ መለያው ነበር። በዘፈኑ ነፃ ሆኖ ተወዛውዞ ታዳሚውም እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል። እሱ ሲዘፍን ቁጭ የሚል የለም . . . እስኪባል ድረስ ሁሉም ታዳሚ ተወዛዋዥ ይሆናል።

እናቱ በሠሩለት ክራር የተፈታው እጁ ሌሎች የሙዚቃ መሣሪያዎችን ለመጫወት አልቦዘነም። ክራርና መሰንቆ ይጫወታል፤ ጊታር ይችላል። እንደውም «ያደ በሌ» የተሰኘውን የኦሮሚኛ ዘፈኑ ቪድዮ የተቀረጸው ከመዝፈን ባሻገር እራሱ ጊታር እየተጫወተ ነው። የሙያ ባልደረቦቹ ሳክስፎንም ይጫወት እንደነበር ይናገራሉ። አማርኛና ኦሮምኛ በደንብ ማወቁ ጠቅሞታል። በሁለቱም ቋንቋዎች ዘፍኖ በርካታ አድማጭ ለማግኘት ዕድል ፈጥሮለታል። ሁለገቡ ሰለሞን በሁለቱም ቋንቋዎች ግጥም ይጽፋል፤ ዜማ ይደርሳል፤ የሙዚቃ መሣሪያዎችን ይጫወታል፤ እንዲሁም ሙዚቃ ያቀናብራል።

እንድ ቦታ ለሙዚቃ ዝግጅት ሲሄድ ከቡድን ጓደኞቹ ተለይቶ የሕዝቡን ባህል ለማወቅ ጊዜ ይወስዳል

ሰለሞን በሄደበት የሄደበትን ሕዝብና ባህል ያከብራል ይላሉ የቀድሞ ባልደረቦቹ። አንድ ቦታ ለሙዚቃ ዝግጅት ሲሄድ ከቡድን ጓደኞቹ ተለይቶ የሕዝቡን ባህል ለማወቅ ጊዜ ይወስዳል። ለዚህም ከኅብረተሰቡ ጋር ጊዜ ያጠፋል። ከዚያም መድረክ ላይ ሲወጣ ሌላ ቋንቋ ቢያቅተው ሰላምታውንና እንደ አስፈላጊው በአካባቢው የሚገኙ የቦታ ሥሞችን በሙዚቃ ውስጥ ያካትታል። «ባቡሪ ከኤ» እያለ የሚዘፍነው ተወዳጅ የኦሮሚኛ ዘፈኑ ነው። ባቡሩ ተነሳ ሆዴ አልችልም ብሎ ካንቺ ጋር ለመግባት ተነስቷል። አንቺ ቆንጆ ልጅ ነፍሴን ወስደሽብኛል፤ እያለ እንዴት አድርጋ ነፍሱን እንደወሰደችበት ይተርካል። ከዚያ እንዳገባት በመግለጽ በሠርጉ ላይ የታደሙ የተለያዩ አካባቢ ልጆች እንዲጫወቱ የአካባቢያቸውን ሥም እያነሳ ያበረታታቸዋል።

የሥራ ባልደረባው የነበሩት አቶ ወንደሰን ቦጋለ ሰለሞን መድረክ ላይ ወጥቶ ገና ባቡሪ ከኤ ሲል የሸላሚው ብዛት ባቡር የመጣ ይመስላል ይላሉ። ሸላሚው እራሱ የመሸለም ተራ እንዲደርሰው ይሰለፋል። ሰለሞን ካለ ጨዋታና ሳቅ ነው ይላሉ። እሱ ለደስታ ለሳቅ ለጨዋታ ቅርብ ነውና አብረውት ያሉ ሁሉ ሳይወዱ በግድ ያስቃቸዋል። ያለውን ማካፈል መለያው ነው። እንደ ጓደኞቹ አስተያየት ሰለሞን ያገኘውን ኪሱ ማሳደር አይችልም። ከሕፃናት ጋር የተለየ መግባባት አለው። የቸገረው ሰው ሲያገኝ ከእሱ አልፎ ከጓደኞቹ አምጡ ብሎ ይረዳል። የተቸገረ አግኝቶ መርዳት ባይችል አብሮ ቁጭ ብሎ የሚያለቅስ፣ ሩህሩህነትን የታደለ ነበር።

ድምጻዊው መልከመልካም፣ ብሎም ዘናጭ ነበር። ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ለየት ያለ የጸጉር ስታይል ጀምሮ ነበር። ቢያጀ ጸጉሩ ከፊት ሙሉ ቁርጥ ሆኖ ከማጅራቱ በላይ የተወሰነ የጸጉሩን ክፍል ያሳድጋል። አንዳንዴም ያደገውን ጸጉሩን ቁጥርጥር ይሠራዋል። ለዚህች ጸጉሩ የተለየ እንክብካቤ ያደርግላት ነበር። ጓደኞቹ ምግብ መራጭ ነው ይሉታል። አብሶ ጥብሳጥብስ ይወዳል። አትክልትም ሌላው ሰለሞን የሚወደው ምግብ ነው። ሽሮ ግን ነብሱ ናት ይላሉ። ጥበበኛም ብቻ ሳይሆን ዕድለኛ የሆነው ሰለሞን 15ሺህ ብር ብዙ በነበረበት ወቅት የ15ሺህ ብር ሎተሪ ዕድለኛም ሆኗል።

ክራር ሠርተው ከሙዚቃ ያቀራረቡት እናቱን ውለታ መርሳት ያልወደደው ሰለሞን እናቱን «ሞገሴ»፣ «አለኝታዬ» ብሎ ዘፍኖላቸዋል።

ብድር ውለታሽን ከምዘነጋው
የጠባሁት ጡትሽ ልሳኔን ይዝጋው
ጸጸት ያናጋኝ

ሰዎች ሌሎቹን በሚረግሙበት ቃል እራሱ እራሱን የእናቱን ውለታ ከዘነጋ ቅጣት እንዲደርስበት በይኗል።

የቤተሰብ ፍቅር በሰለሞን ዘፈኖች ውስጥ የቅድሚያ ትኩረት ከሚጣቸው ተርታ ይገኛል። እነሱን ከማጽናናት ባለፈ የነሱ ናፍቆት ምን እንዳደረገው ይተርካል። በአብዛኛው በሀገራችን የሚዘፈኑ ዘፈኖች አንዱን የቤተሰብ አካል ነጥሎ ቢሆንም፣ እሱ ግን ሙሉ ቤተሰቡን ቢለያዩም ደህና መሆኑን የሚያበስርበት ዘፈን አለው።

እምባሽ አይፍሰስ
እምዬ እምባሽ አይፍሰስ
አልሞትኩም አለሁ በጤና
አባቴ ሀሳብ አይግባህ
ብርቅም አለሁ በጤና
እህቴም አይዞሽ አይከፋሽ
አልሞትኩም አለሁ በደህና

እያለ መላው ቤተሰቡን የተራራቁ መገናኘታቸው እንደማይቀር ያበስራቸዋል።

ድምጻዊው ሀገሩን «ካንቺ ያስቀድመኝ» ይላታል። የሰለሞን ለየት ያለው ችሎታውና በዚህ ዘፈንም የሚታየው ድምጹን እንደአስፈላጊነቱ መቀያየሩ ነው። በዚህ ዘፈንም የጀግናው አባቱን ኑዛዜ በዜማ ቀይሮ ሲያቀርብ ድምጹን የትልቅ ሰው አድርጎ ነው።

አሁን አርጅቻለሁ ልጄ
ዕድሜዬ እየገፋ ሄደ
ሀገርህን አይዞሽ በላት
ካንተ ወዲያ ሰውም የላት

የሚሉት አባት የሁሉም አባት ያስተላለፉት አደራ ስለሚመስል ሁሉንም አጀግኖ የሀገር ባላደራነት ላይ ያስቀምጣል። ሀገርን ያገለገሉ ጀግና አባት ልጃቸው ኑዛዜያቸው ትዝ ሲለው፤

አርጅቻለሁ በቃ ሲለኝ
ከሞት አፋፍ ቆሞ ሲያየኝ
ወራሼ ነህ አይዞህ ሲለኝ
ክንዴ መክኗል በቃ ያለኝ ......
ውል አለብኝ ቃል አለብኝ (2 ጊዜ)
ለዚች ሀገር ለዚች አድባር
ለዚች መሬት ለዚች ሀገር
እስቲ በሉ በሉ በሉ

ብሎ ለሀገሩ ሀሳቡን የሚገልጽበት ቃል ቢያጥረው፣ ቃላት ቢረከሱበት እናቶች ልጆቻቸውን የሚያስተኙበትንና የሚያጫውቱበትን ቃል ተጠቅሞ ሀገሩን ዳግም ወልዶ እሹሩሩ ብሏታል። ሀገሩ እሱ እያለ ምንም እንደማትሆን ሀሳቧን ጥላ እንድትተኛ ሲያባብላት እሹሩሩ፡-

የከዳሽ ይከዳ የጎዳሽ ይጎዳ
እሹሩሩሩሩ
የጎዳሽ ይጎዳ የከዳሽ ይከዳ


«ዋሄ በሬዴኬ» የተሰኘው የኦሮሚኛ ዘፈኑ ቋንቋውን በማይችሉት ዘንድ ጭምር እጅግ ተወዳጅ የሆነ የሰለሞን ሥራ ነው። በዘፈኑ «ያ ሻማ ቡሬ ኪያ» ቡሬ ሻማ የምትለብስው ልጅ ስለ ቁንጅናሽ ከሰፈር ነው የሰማሁት። ዓይን የለውም ይላሉ የሚያሳበድ ነው። የልጅቷ ፍቅር ምኑም አይታወቅ። ለማነው የምነገረው ይህ አስቸጋሪ ነገር ነው። እያለ ፍቅር ዓይን እንደሌለው የገለጸበት ነው።

ሰለሞንና እንቁጣጣሽ ቁርኝታቸው የተለየ ነው። ከስርቅታዬ ውጪ እንደስርቅታዬ ባይጎላም በዓልን ፍቅር በፍቅር እናክብር የሚልበት «ፍቅር በፍቅር» የተሰኘ ዘፈን አለው። በዘፈኑ የድሮው ትዝታውን የአባቶችን ስሜትና ምርቃትንና የልጃገረዶችን «እታበባዬ» ህብረ ዝማሬ አካቷል። ይሄም ዘፈኖች እንደ ስርቅታዬ ሁሉ በሚቀበሉት ሴቶች የታጀበ ነው። ሰለሞን ሀገረኛ ግጥምና ዜማ ከአዲስ ግጥምና ዜማዎች ጋር ማዋሀድ መታወቂያው ነበር። በወጣትነቱ የተለየነው ድምጻዊ ሰለሞን ደነቀ ከሞተ 20 ዓመታትን ተሻግሯል። ግን በሥራው ሕያው እንደሆነ ቀጥሏል።

# ዓለም አቀፍ

## የጋቦን አዲስ ገዥዎች የዴሞክራሲ መስተጓጎል ጊዜያዊ ነው አሉ

በጋዜጣው ሪፖርተር



የጋቦን አዲስ ወታደራዊ መንግሥት ዴሞክራሲን እንደሚመልስ ቃል ገብቷል።

የመንግሥት ግልበጣው መሪ ጀኔራል ብሪክ ኦሊጉ ኑጉማ የሀገሪቱ ዴሞክራሲ ተሻሽሎ እንደሚመልስና መስተጓጎሉም ጊዜያዊ መሆኑን ገልጸዋል።

ሆኖም የሀገሪቱ ተቃዋሚዎች ጥምረት ወታደራዊ መንግሥቱ ሥልጣን ለሕዝባዊ መንግሥት ለማስረከብ ምልክት እያሳየ አይደለም ሲሉ ወቅሷል። አርብ በቴሌቪዥን መስኮት የቀረቡት ጀኔራሉ መንግሥታቸው በፍጥነት እንደሚሠራ ገልጸው፤ ነገር ግን አንድ ዓይነት ሰዎችን ሥልጣን ላይ ያቆየ ምርጫ በማድረግ ተመሳሳይ ስህተት እንደማይሠሩ ተናግረዋል።

ከሰሞኑን የተካሄደው ምርጫ ትክክለኛ አሸናፊ ነኝ የሚለው ተቃዋሚ ጥምረት፤ በጋቦን ሕዝባዊ አስተዳደር እንዲመለስ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ እንዲወተውት ጥሪ አቅርቧል። ጀኔራል ብሪክ ኦሊጉ ኑጉማ የጋቦን አዲስ መሪ ሆነው ሰኞ ቃለ መሀላ እንደሚፈጽሙ ተነግሯል። ፕሬዚዳንት አሊ ቦን የቤት ውስጥ እስረኛ መደረጋቸውም ተገልጿል።

የጋቦን መፈንቅለ መንግሥት ከ2020 ወዲህ በምዕራብና ማዕከላዊ አፍሪካ የተደረገው ስምንተኛው መንግሥት ግልበጣ ነው። የጋቦን መፈንቅለ መንግሥት በመንግሥታቱ ድርጅት፣ በአፍሪካ ኅብረትና በሀገሪቱ የቀድሞ ቅኝ ገዥ ፈረንሳይ ተወግዟል።

ከ2020 ወዲህ በማዕከላዊ አፍሪካ በኒጀር፣ ማሊ፣ ጋያና፣ ቡርኪና ፋሶ እና ቻድ መፈንቅለ መንግሥት ተደርጓል።

የአፍሪካ ኅብረት እና የአውሮፓ ኅብረት አውግዘውታል። ከ2009 ጀምሮ ሥልጣን ላይ የነበሩት አሊ ቦንጎ በቁም እስር ሳሉ «ወዳጆቼ ድምጻችሁን አሰሙ» ብለዋል።

ሆኖም ግን ከሥልጣን በመወገዳቸው የሀገሪቱ ዜጎች ደስታቸውን ሲገልጹ ተስተውሏል።



## ሩሲያ ከዩክሬን ወደ ግዛቷ ስጠቀለለቻቸው አራት ግዛቶች ልማት 20 ቢሊዮን ዶላር መደበች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሩሲያ ባለፈው ዓመት ወደ ግዛቷ ላካተተቻቸው አራት ግዛቶች ልማት የሚውል 20 ቢሊዮን ዶላር መድባለች።

ፕሬዚዳንት ፑቲን እንደገለጹት፤ ሩሲያ በሚቀጥሉት ሁለት ከግማሽ ዓመታት በሚሆን ጊዜ ውስጥ በግዛቶቹ ለሚተገበር ልማት ከፌዴራል በጀት 20 ቢሊዮን ዶላር ይመደባል ብለዋል።

ሩሲያ ሁሉንም ግዛቶች ሙሉ በሙሉ ያልተቆጣጠረች ሲሆን፣ ባለፈው ዓመት ግዛቶቹን ለመጠቅለል ያሳለፈችው ውሳኔም በተለይም ከምዕራባውያን ውግዘትን አስከትሎባታል።

ፑቲን ግዛቶቹን ወደ ሩሲያ ባጠቃለሉበት ወቅት እንደተናገሩት፣ በአራቱ ግዛቶች ላይ የሚደርስ ማንኛውም ጥቃት በሩሲያ ላይ እንደተቃጣ ይቆጠራል። ሩሲያ ኬርሶን፣ ዛፖሬዥየ፣ ዶምባስ እና ሉሀንስክ ግዛት ወደ ግዛቷ የጠቀለለችው በሕዝበ ውሳኔ ነው ብትልም ዩክሬን እና ምዕራባውያን የሀሰት ሕዝበ ውሳኔ ነው ብለውታል።

በምዕራባውያን የምትደገፈው ዩክሬን እና ሩሲያ እያደረጉት ያለው ጦርነት አሁንም እንደቀጠለ ነው።

የዋይት ሃውስ የደህንነት ቃል አቀባይ ጆን ከርቢ እንዳሉት፣ በዛፖሪዝሂያ በስተደቡብ በኩል የዩክሬን ጦር በባለፉት 72 ሰዓታት ውስጥ ድሎችን ተቀናጅቷል ብለዋል።

የዩክሬን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዲሚትሮ ኩሌባ የዩክሬን ኃይል እየገሰገሰ ቢሆንም «ጠንካራ ውጊያ እየተካሄደ ነው» ሲሉ ለሲኤኤን ተናግረዋል።

ሩሲያ በበኩሏ በዩክሬን ሰሜን ምሥራቅ በምትገኘው በኩፒያንስ ከተማ አቅራቢያ ቁልፍ ስትራቴጂካዊ ኮረብታማ ስፍራ ተቆጣጥሬያለሁ ብላለች።


### የኮምፒውተር እና የተለያዩ የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች (Office Machine) ግዥ ማስታወቂያ

### ጨረታ ቁጥር EMPDE/NCB/06/2015

ድርጅታችን የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻ እና ማከፋፈያ ድርጅት ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ኮምፒውተር እና የተለያዩ የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች (Office Machine) ግዥ ለመፈጸም ብቃት ያላቸው አስመጪ እና አከፋፋይ ድርጅቶችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

በመሆኑም በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የሚከተሉትን ነጥቦች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይጠበቅባቸዋል፡፡

1. የታደሰ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ፣ የታክስ ክሊራንስ ደብዳቤ፣ የተ.እ.ታ ምዝገባ ሰርተፊኬት፣ የግብር ከፋይ ሰርተፊኬት እና የአቅራቢ ምዝገባ ሰርተፊኬት ማቅረብ የሚችሉ፤
2. ስለጨረታው ዝርዝር ሁኔታ የሚገልጸውን ሰነድ የማይመለስ ብር 300 /ሦስት መቶ ብር/ በመክፈል ከትም/መሳ/ማም/ማከ/ድርጅት ዘወትር በሥራ ሰዓት ከጠዋት 2፡00 ሰዓት እስከ 6፡30 ሰዓት እንዲሁም ከ7፡30 ሰዓት እስከ 10፡30 ሰዓት ከቢሮ ቁጥር 35 መውሰድ ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች የጨረታ ዋስትና ብር 100,000.00 (አንድ መቶ ሺህ ብር) በሲፒኦ ወይም በባንክ ጋራንቲ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
4. ጨረታው መስከረም 10 ቀን 2016 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ተዘግቶ በተመሳሳይ በዚሁ እለት ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በሚገኙበት ይከፈታል፡፡
5. ከላይ የተዘረዘሩትንና በጨረታ ሰነዱ ውስጥ የተመለከቱትን ግዴታዎች የምታሟሉ ድርጅቶች በጨረታው መሳተፍ ትችላላችሁ፡፡
6. ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለበለጠ መረጃ ስልክ ቁጥር፡- 0116 -46-34 81

**የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻ እና ማከፋፈያ ድርጅት**

### ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

### የግልጽ ጨረታ ቁጥር NCB/OEB/GOV/04/2016

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ለባሌ ሮቤ እና ሓራማያ ራዲዮ ትምህርት ፕሮግራም ጣቢያ ጀኔሬተር ብቃት ያላቸውን ድርጅቶች በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ **በዚሁ መሠረት**፡- ከላይ የተጠቀሰውን ሁለት(2) ጀኔሬተር ባሌ ሮቤ እና ሓራማያ ራዲዮ ትምህርት ፕሮግራም ጣቢያ ድረስ በማድረስ፣ በመትከል፣ በማሰልጠንና አስፈላጊውን መለዋወጫ ማቅረብ የምትችሉ ተጫራቾች ከጨረታው ሰነድ ጋር፡-

- በዘመኑ የታደሰ እና በዘርፉ አግባብነት ያለው ሕጋዊ ንግድ ፈቃድ፣ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡበት ሰርተፊኬት፣ የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር፣ በጨረታ ለመሳተፍ የሚያስችል ደብዳቤ (clearance) ፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉበት ማስረጃ እና በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገቡበትን ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቢሮ አንደኛ ፎቅ የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ) በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ንግድ ባንክ አካውንት(Oromia Education Bureau B.Ac.No. 1000007342121) በመክፈልና ደረሰኝ በማቅረብ የጨረታ ሠነዱን ዘወትር በሥራ ሰዓት መግዛት ይችላሉ፡፡
- ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ C.P.O ወይም የባንክ ጋራንቲ (Unconditional Bank Guarantee ) 30,000.00 (ሠላሳ ሺህ) በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ (Oromia Education Bureau) ስም የተዘጋጀ ማቅረብ አለባቸው ::
- ተጫራቾች የዕቃውን ዝርዝር ነጠላ ዋጋ እና ከቫት ጋር ከጨረታ ሰነዱ ጋር አባሪ አድርገው በተሰጠው ስፔስፊኬሽን መሠረት በመሙላትና የድርጅቱን ማህተምና ፊርማ በሁሉም ገፆች ላይ በማሳረፍ ፋይናንሻል ኦሪጅናል፣ ቴክኒካል ኦሪጅናል፣ ፋይናንሻል ኮፒ፣ ቴክኒካል ኮፒና C.P.O ወይም ባንክ ጋራንቲ (un conditional Bank Guarantee ) ለብቻ በፖስታ ከታሸገ በኋላ በመጨረሻ ሁሉንም በአንድ ፖስታ ታሽጎ ከሳር ቤት ወረድ ብሎ በሚገኘው የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ 1ኛ ፎቅ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
- ተጫራቾች ሙሉ አድርሻቸውን፣ስልክ ቁጥራቸውንና የጨረታ ቁጥሩን በፖስታው ላይ በመጥቀስ የጨረታ ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ16ኛው የሥራ ቀን እስከ 8፡00 ሰዓት ለዚሁ በተዘጋጀ ሳጥን ውስጥ ሰነዱን በማስገባት 8:00 ሰዓት ላይ ተዘግቶ በዚሁ ዕለት በ8፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
- ቢሮው የተሻለ ዘዴ ወይንም አማራጮች ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብት አለው::

**አድራሻ**፡- ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ከሳርቤት አደባባይ ወደ ቄራ መሄጃ ወረድ ብሎ ስ.ቁ 0113717973

**የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ**

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ድርድሩ በሕዳሴው ያስመለስነውን ጂኦፖለቲካዊ ከፍታ የሚያዘልቅ ይሁን፤

**(ክፍል አንድ)**

ምስጋና ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይግባና ግድቡ ከለየለት ክሽፈት ድኖ ዛሬ ላይ አፈጻጸሙ 90 በመቶ ደርሷል። 540 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይልም ማመንጨት ችሏል። ለአራተኛው ዙር ውሃ ሙሊትም እየተዘጋጀ ነው። ከሁሉም ከሁሉም በላይ ግን እንደ ቬኒዞላ ገንዘብ «ቦሊቫር» ጋሽቦ የነበረውን የሀገራችንን ስትራቴጂካዊ ይዞታ በሕዳሴው ደንደስ መመለስ ተችሏል። ከምንም ነገር በላይ ከግብጽ ጋር የሚደረግ ድርድር ይሄን የጂኦፖለቲካ ከፍታ የሚያስጠብቅ ፣ የሚያጸናና የሚያዘልቅ ሊሆን ይገባል የሚል ጽኑ እምነት አለኝ። ወደ ሰሞነኛው የካይሮ ድርድር ከመመለሴ በፊት ስለ ጂኦፖለቲክስ ትንሽ ልበል።

ቀለል ባለ አገላለጽ ጂኦፖለቲክስ ማለት ከዓለምአቀፍ ግንኙነት አንጻር ወይም አኳይ የጂኦግራፊንና የፖለቲካን ግንኙነት ማጥናት ነው። የሀገራችን ድንበር፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ የሕዝብ አሰፋፈር፣ የእድገት ደረጃ፣ የምታራምደው የፖለቲካ ሥርዓትና ወታደራዊ አቅም የሀገራችንን የጂኦፖለቲክስ ይወስናል። የሀገራችን የሕዝብ ብዛትና የተፈጥሮ ሀብት ጂኦፖለቲክሷን ከፍ ሲያደርጉት በአንጻሩ የሀገሪቷ ውስጣዊ አንድነት ደካማ መሆን ጂኦፖለቲካዊ ስፍራዋን ወይም ዋጋውን ያሳንሰዋል። የሕዳሴው ግድብ መጠናቀቅ ደግሞ ጂኦፖለቲካዊ ቦታዋን ከፍ ያደርገዋል።

የዐረቡ ዓለም የነዳጅ ባለቤት መሆኑ ከተረጋገጠ፣ እኤአ በ1948 ዓ.ም እሥራኤል የአይሁዶች መንግሥት ሆና ከቆመች፣ ከ1993 ዓ.ም የመስከረም 1 ቀን የሽብር ጥቃት በኋላ የአሜሪካ፣ የምዕራባውያንና የዓለምአቀፉ ተቋማት የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ ማጠንጠኛ ነዳጅ፣ የእሥራኤል ደህንነት እና የጸረ ሽብር ዘመቻ ሆነ። ዛሬ እንዲህ ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ሁኔታ ወደ ቻይናና ራሽያ ሊወሰድ።

ሆኖም ለቆየው የአሜሪካ የውጭ ግንኙነት ፖሊስ እና ስትራቴጂ ተግባራዊነት ከዐረቡ ዓለም ግብፅ ቀዳሚዋ ስትራቴጂካዊ አጋር ሆና ተመርጣለች። ግብፅን ተመራጭ ያደረጋት ለምዕራባውያን የጡት ልጅ እሥራኤል ጎረቤት መሆኗ፤ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጧ በተለይ የስዊዝ ቦይ ባለቤት መሆኗ፤ የእስላማዊ ትምህርት ማዕከል እና የዐረብ ብሔርተኝነት አቀንቃኝ መሆኗ፤ ዜጎቿ ከሌላው የዐረብ ዓለም ጋር ሲነጻጸር በዓለማዊም ሆነ በእስላማዊ ትምህርት የገፉ በመሆናቸው በአጠቃላይ በነበራት ጂኦፖለቲካዊ በምዕራባውያንም ሆነ በእስላማዊው ዓለም ዘንድ ሞገስ አግኝታለች።

ይህን ሞገሷን የዐረቡን ዓለም ጨምሮ የዐረብ ሊግን እንዳሻት ለማሽከርከር ትጠቀምበታለች። በልዩነትና በክፍፍል ከሚንጠራወዘው የዐረቡ ዓለም ግብፅ እንደ ሰንደቅ ከፍ ብላ እንድትታይ ረድቷታል። ይህን መከፋፈል እሥራኤልን ጨምሮ አሜሪካውያን ሆኑ ምዕራባውያን ይፋ ባያወጡትም የሚደግፉት ስለሆነ ግብፅ ሽብልቅ ሆና እንድታገለግል (ብድርና እርዳታ እየሰጡ በአናቱ የጦር መሣሪያ እስካፍንጫዋ እያስታጠቁና ወታደራዊ ሥልጠና እየሰጡ ይንከባከቧታል። አሜሪካ ብቻ በየአመቱ ወደ 4 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ የጦር መሣሪያ፣ የወታደራዊ እርዳታና የልማት ድጋፍ ታደርጋለች።

ግብፅ በአጠፋው ይህን ውለታ ከግምት ያስገባ እና እኤአ በ1979 በአንዋር ሳዳትና በእሥራኤል መካከል የተፈረመውን የሰላም ስምምነት መሠረት ያደረገ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ቀርጻለች። የሀገሪቱን ኢኮኖሚ፣ ደህንነትና ፖለቲካ በመዳፉ የጠቀለለው የግብፅ ጦርና ደህንነት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን ተግባራዊነት ያረጋግጣል በዓይነ ቁራኛ ይከታተላል። ዘብ ሆኖ ሌት ተቀን ከዐረቡ አብዮት

> **የኢትዮጵያ ተደራዳሪ ወገን፣ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ለኢትዮጵያ የሚሰጠውን ጥቅምና በቀጣይ የዓባይ ውኃ ፍትሐዊና ምክንያታዊ አጠቃቀምን በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲሁም በቀጣናው ሀገሮች መካከል ትብብርን በሚያጎለብት መልኩ እየሠራ ነው**

በኋላ በምርጫ የፈርኦኖችን በትረ ሥልጣን ጨብጠው የነበሩ የመጀመሪያው የእስላም ወንድማማቾቹ አባል ፕሬዚዳንት ሞሐመድ ሙርሲ እንኳ የድርጅታቸውንም ሆነ አክራሪ እስላሞች ግፊት ተቋቁመው የግብፅና እሥራኤልን የሰላም ስምምነት ማክበር ችለዋል ።

መጀመሪያ በመፈንቅለ መንግሥት በኋላ በምርጫ ወደ መንበሩ የመጡት ፕሬዚዳንት አብዱልፈታህ አልሲሲም ከሳዳት፣ ከሙባረክና ከሙርሲ በላይ የሰላም ስምምነቱን እያስፈጸሙ ነው። የእሥራኤል ጉዳይ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያቸው ቀኖና ነው ማለት ይቻላል። ከእሥራኤል ጀርባ ደግሞ አሜሪካ አለች። ግብፅ ናይል የህልውናዬ ጉዳይ ነው ብላ በሕገ መንግሥቷ ብታካትተውም፤ በውስጠ ታዋቂ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዋ የማዕዘን ራስ ቢሆንም በግላጭ ትኩረቱ እሥራኤል፣ ፍልስጤምና አሜሪካ ላይ ነው።

ግብፅ ዓባይን ከምንጩ ለመቆጣጠር፣ ሀገራችንን ቅኝ ለመግዛት እና ጠንካራ ሉዓላዊ ሀገር ሆና እንዳትወጣና ይህ ቀን ( ዓባይ የሚገደብበት ቀን ) እውን እንዳይሆን ከ11 ጊዜ በላይ ወራናለች። በስውር ደግሞ ምን አልባት ለሺህ ወይም ለሚሊዮን አመታት አሲራለች። በተለይ ከ20ኛው መክዘ ወዲህ ደግሞ የተለያዩ ኃይሎችን በመጠቀም የውክልና ( proxy ) ጦርነት በማካሄድ ሀገራችንን ስታዳክም ኖራለች። ይህ እኩይ ዓላማዋ ከሞላ ጎደል በመሳካቱ የቤት ሥራዋን በማጠናቀቋ ዝቅ አድርጋ ስታየን ኖራለች።

ከታሪካዊዋ ሐምሌ 15 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ግን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሁኔታዎች ተቀይረዋል። በሴራና በደባ በቀጣናውም ሆነ በዓለምአቀፍ መድረክ ያሳጣችን ጂኦ ፖለቲካዊ እና ስትራቴጂካዊ ስፍራ ከ30 አመታት በኋላ መልሰን ተረክበናል። ምርኳችን ተመልሷል። የቀጣናው ጂኦ ፖለቲካዊ አሰላለፍ በታላቁ የሕዳሴ ግድብ እንደ አዲስ ተበይኗል። ተፐውዟል። የምለው ለዚህ ነው ። ከዚህ በኋላ የሀገራችን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታና ጂኦ ፖለቲካዊ ስፍራ ከ1983 ዓ.ም በፊት ወደነበረው ከመመለሱ ባሻገር ከግብፅ የሚተናነስ አይደለም። ገና ዛሬ ታዋቂው የግሪክ የታሪክ ሰው ሔሮዶተስ እንዳለው ግብፅ የዓባይ (የኢትዮጵያ) ስጦታ ሆነች ። ስለ ጂኦፖለቲክስ አንድምታ ይህን ያህል ካልሁ ወደ ሰሞነኛው ድርድር ልመለስ።

የኢትዮጵያ የአሁኑም ሆነ የወደፊት ትውልዷን በዓባይ ውኃ የመጠቀም መብት አሳልፋ እንደማትሰጥ የታላቁ ሕዳሴ ግድብ የኢትዮጵያ ተደራዳሪዎች በድጋሚ ማረጋገጣቸውን፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን የመጀመሪያ ሙሌትና ውኃ አለቃቀቅ በተመለከተ በኢትዮጵያ፣ ግብፅና ሱዳን መካከል በግብፅ ካይሮ ከተማ ከነሐሴ 21 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ለሁለት ቀናት የተካሄደው አዲስ ድርድር የመጀመሪያ ምዕራፍ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ የሦስቱ ሀገሮች ተደራዳሪዎች ቀጣዩን ዙር ውይይት በአዲስ አበባ ለማድረግ ቀጠሮ መያዛቸውንና የኢትዮጵያ ተደራዳሪ ቡድንም ባለፈው ማክሰኞ ነሐሴ 23 ቀን 2015 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መመለሱን የአማርኛው ሪፖርተር ዘገባ ያስረዳል።

የሦስቱ ሀገሮች አዲስ ድርድር ባለፈው እሑድ ነሐሴ 21 ቀን 2015 ዓ.ም በግብፅ ካይሮ ከተማ ሲጀመር የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ተደራዳሪ ቡድን መሪና በአሜሪካ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን አምባሳደር የሆኑት ስለሺ በቀለ (ዶ/ር)፣ የሦስትዮሽ ድርድሩ በሦስቱ ሀገሮች መካከል ትብብርን ለማጠናከር እንደሚረዳ መግለጻቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ድርድሩ በተጀመረበት ዕለት ባወጣው መግለጫ አስታውቋል።

አምባሳደር ስለሺ(ዶ/ር) ፣ «የኢትዮጵያ የአሁንና የወደፊት ትውልድ በዓባይ ውኃ የመጠቀም መብትና ጥቅም» መሠረታዊ መሆኑን አጽንኦት ሰጥተው መናገራቸውን፤ በተጨማሪም ግድቡ ለሦስቱ ሀገሮች የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ መሆኑንና ኢትዮጵያ በፍትሐዊና ምክንያታዊ ተጠቃሚነት መርህ ላይ የተመሠረተ አቋሟን አጠናክራ ድርድሩ ሁሉንም በሚያግባባ መልኩ እንዲጠናቀቅ እንደምትሠራ ገልጸዋል።

አምባሳደር ስለሺ በካይሮ የተካሄደው ድርድር ከተጠናቀቀ በኋላ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክትም ይህንኑ የጠቆሙ ሲሆን፤ በኢትዮጵያ፣ ግብፅና ሱዳን መካከል ለሁለት ቀናት ሲካሄድ የነበረው የታላቁ ሕዳሴ ግድብ የመጀመሪያ ሙሌት (ግድቡ በጥቂት ዓመታት ሙሉ ደረጃ እስኪደርስ ያለውን) እና የግድቡ የውኃ አለቃቀቅን የተመለከተው ድርድር ነሐሴ 22 ቀን መጠናቀቁን፣ ካይሮ ላይ በተካሄደው ድርድር ያልተሸፈኑና ስምምነት ባልተደረሰባቸው በርካታ የስምምነት አንቀጾች ላይ ሁለተኛ ዙር ድርድር በመጪው መስከረም ወር 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ ሁለተኛ ዙር በማድረግ ወደ ስምምነት ለመድረስ ቀጠሮ መያዙን ጠቁመዋል።

«የኢትዮጵያ ተደራዳሪ ወገን፣ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ለኢትዮጵያ የሚሰጠውን ጥቅምና በቀጣይ የዓባይ ውኃ ፍትሐዊና ምክንያታዊ አጠቃቀምን በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲሁም በቀጣናው ሀገሮች መካከል ትብብርን በሚያጎለብት መልኩ እየሠራ ነው ።» በግድቡ ዙሪያ የተካሄደው የሁለት ቀናት ድርድር መጠናቀቁን አስመልክቶ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ባወጣው መግለጫም፣ ኢትዮጵያ በፍትሐዊና ምክንያታዊ መርህ መሠረት የራሷን ድርሻና ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ ድርድሩ በስምምነት እንዲቋጭ ጥረቷን እንደምትቀጥል አስታውቋል።

በአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ የውኃ ምሕንድስና መምህርና የኢትዮጵያ ተደራዳሪ ቡድን አማካሪ የሆኑት ይልማ ስለሺ (ፕሮፌሰር) ማክሰኞ ነሐሴ 22 ቀን በአልጀዚራ የቴሌቪዥን ጣቢያ በተደረገ የሦስቱ ሀገሮች ባለሙያዎች ክርክር ተሳትፈው፣ ስለአጠቃላይ የድርድሩ ሒደት ባደረጉት ገለጻ፣ ሦስቱ ሀገሮች ቀደም ሲል ባደረጓቸው ድርድሮች የታላቁ ሕዳሴ ግድብ የውኃ ሙሌትን በተመለከተ ያለ ልዩነት ስምምነት ላይ መድረሳቸውንና አሁን በተጀመረው አዲስ ድርድር የግድቡ የውኃ ሙሌት ሊያከራክር እንደማይችል አመልክተዋል፣ ሦስቱ ሀገሮች ከዚህ ቀደም ባደረጓቸው ድርድሮች የሕዳሴ ግድቡ የውኃ ሙሌት ከአምስት እስከ ሰባት ዓመታት ባለው ጊዜ ውስጥ እንዲከናወንና በውኃ ሙሌቱ ወቅት የድርቅ ሁኔታ ያጋጠመ እንደሆነ ኢትዮጵያ ውኃ እንደማትይዝ ተነጋግረው ያለ ልዩነት መስማማታቸውን አስታውሰዋል።

ነገር ግን በሦስት ሀገሮች ድርድር ላይ አስቸጋሪ የሆነው የግድቡ ዓመታዊ ኦፕሬሽን ማለትም የግድቡ የውኃ አለቃቀን የተመለከተው ጉዳይ ነው። ይህንን አከራካሪ ጉዳይ በተመለከተ በግብፅ በኩል የሚቀርበው ጥያቄ ለሚቀጥሉት ሁለት አሥርት ዓመታት ከሕዳሴ ግድቡ በየዓመቱ የሚለቀቀው የውኃ መጠን ምን ያህል እንደሚሆን በቁጥር እንዲገለጽና ለዚህም ኢትዮጵያ በውል የታሰረ ዋስትና እንድትሰጥ በግብፅ በኩል አቋም መያዙን ይልማ ስለሺ (ፕሮፌሰር) ተናግረዋል። ይህ የግብፅ ጥያቄ በሌላ አገላለጽ ኢትዮጵያ ከሕዳሴ ግድቡ በላይ ባሉ አካባቢዎች ወይም በዓባይ ገባር ወንዞች ላይ ሌላ ተጨማሪ ልማት ማካሄድ የምትችለው ግብፅና ሱዳንን አሳውቃና ሁለቱ ሀገሮች የሚያገኙት የውኃ መጠን እንደማይቀንስ መረጋገጥ አለበት ማለት ነው ብለዋል።

ምክንያታቸውን ሲያስረዱም፣ ግብፅ የምትጠይቀው የዓባይ ውኃ ድርሻ እ.ኤ.አ. በ1959 ከሱዳን ጋር የተደረገውን የቅኝ ግዛት ውል በመጥቀስ ሲሆን፣ ይህ በሁለቱ ሀገሮች መካከል ብቻ የተደረገው ውል የዓባይ ውኃ ምንጭና ተፈጥሯዊ ባለቤት የሆነችውን ኢትዮጵያን ከማግለሉ በተጨማሪ ለኢትዮጵያ ምንም ዓይነት የውኃ ድርሻ የማይሰጥ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

ኢትዮጵያ ይህንን ፈጽሞ ልትቀበል አትችልም ያሉት የተደራዳሪ ቡድኑ አማካሪ ስለሺ ይልማ (ፕሮፌሰር)፣ ምክንያታቸውን ሲያስረዱም «በአንድ በኩል የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚጋፋ በመሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጥያቄው በቋንቋ አጠቃቀም ተሸፍኖ የቀረበ የውኃ ክፍፍል ጥያቄ በመሆኑ ነው ብለዋል። ይህ የሦስትዮሽ ድርድር እንደ አዲስ እንዲጀመር የተወሰነው ከአንድ ወር በፊት የሱዳንን ፖለቲካዊ ችግር ለመፍታት በግብፅ በተካሄደው ጉባዔ ለመሳተፍ ወደ ሥፍራው ያቀኑት ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከጉባኤው ጎን ለጎን ከግብጹ አቻቸው ፕሬዚዳንት አብዱል ፈታህ አልሲሲ ጋር ከተወያዩ በኋላ ነው። ሁለቱ መሪዎች ባደረጉት በዚህ ውይይት የሕዳሴ ግድቡን ድርድር ዳግም ለማስጀመርና በአራት ወራት ውስጥ ለማጠናቀቅ መስማማታቸውን በጋራ ባወጡት መግለጫ ማስታወቃቸው ይታወሳል።

ሁለቱ መሪዎች የሕዳሴ ግድቡን ድርድር በአራት ወራት ለማጠናቀቅ መስማማታቸውን በይፋ መግለጻቸውን ተከትሎ ሪፖርተር ያነጋገራቸው የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ተደራዳሪና የባለሙያዎች ቡድን ሰብሳቢ የሆኑት ጌድዮን አስፋው (ኢንጂነር)፣ ነገሩ ድንገተኛና እርሳቸው የማያውቁት ቢሆንም እስካሁን ስምምነት እንዳይደረስ ያደረገውን ክርክር ግብጾች ይዘው የማይቀርቡ ከሆነ በአራት ወር ባይሆንም በአጭር ጊዜ ስምምነት ላይ መድረስ እንደሚቻል ገልጸው ነበር።

በግብፅ በኩል የሚነሳውና ስምምነት እንዳይደረስ ምክንያት የሆነው የክርክር ነጥብ በ1959 በተደረገውን የዓባይ ውኃ ክፍፍል ያገኙችውን ድርሻ እንዲጠበቅ፣ በሌላ አነጋገር ኢትዮጵያ ከሕዳሴው ግድብ በኋላ በዓባይ ውኃ ላይ ምንም ዓይነት ልማት እንዳታካሂድ መቅረባቸው እንደሆነ የጠቀሱት ጌድዮን አስፋው (ኢንጂነር)፣ ግብፅ ይህንን ክርክር ከተወች በአጭር ጊዜ ስምምነት ላይ መድረስ እንደሚቻል አስረድተዋል።

ሻሎም ! አሜን ።

# ስፖርት



# ከማራቶን ቻምፒዮኖቹ አንደበት

ብርሃን ፈይሳ

በዓለም ቻምፒዮና መድረክ የሴቶች ማራቶን ድል እኤአ ከ2015 የቤጂንግ ቻምፒዮና ወዲህ ፊቱን ወደ ኢትዮጵያ መልሷል። ቤጂንግ ላይ በአትሌት ማሬ ዲባባ የተገኘው የማራቶን ድል ባለፉት ሁለት ቻምፒዮናዎችም በተከታታይ የኢትዮጵያውያን አትሌቶች ሆኗል። 2022 ላይ ጎተይቶም ገብረሥላሴ፣ 2023 ላይ አማኔ በሪሶ በድሉ ደምቀዋል።

የዘንድሮውን የተለየ የሚያደርገው ኢትዮጵያውያን በማራቶን ታሪክ አረንጓዴ ጎርፍ ለመሥራት እስከመጨረሻ ያደረጉት ጥረት ነው። ይህ ጥረት አትሌት ያለምዘርፍ የኋላው በመጨረሻው ኪሎ ሜትር በመድከሟ ለጥቂት ባይሳካም አንደኛና ሁለተኛ ደረጃን ይዘው በማጠናቀቅ በርቀቱ ደማቅ ታሪክ ተፅፏል። አማኔ ቡዳፔስት ላይ ወርቁን አጥልቃለች፣ የአምናዋ ቻምፒዮን ጎተይቶም ደግሞ ያለፈው የወርቅ ሜዳሊያ ላይ የብሩን ሜዳሊያ ደርባለች።

አዲሷ ቻምፒዮን አማኔ ቡዳፔስት ላይ የተሠራው አኩሪ ገድል ከዝግጅት ጀምሮ የነበረው የቡድን ሥራ ውጤት መሆኑን ከኢፕድ ጋር በነበራት ቃለምልልስ ተናግራለች። ‹‹እዚህ ስንዘጋጅ የነበረው በቡድን እንደመሆኑ በውድድሩ ላይም በአንድነትና በመደጋገፍ ነበር የሮጥነው። በቡድኑ የተካተቱት በማራቶን ምርጥ የሚባሉ አትሌቶች መሆናቸውም ለድሉ ረድቶናል›› ትላለች አማኔ። ያለፉትን ዓመታት በጉዳት ማሳለፏን የምታስታውሰው አዲሷ የማራቶን ንግሥት፤ በቻምፒዮናው አሸንፋ ባንዲራዋን ለማውለብለብ በመብቃቷ ደስታዋ ወደር



ፎቶ- እዮብ ተፈራ

አትሌት አማኔ በሪሶ፣



አትሌት ጎተይቶም ገብረሥላሴ፣

የለውም። ‹‹ፈጣሪም በዚህ ክሶኛልና ስኬታማ ስላደረገኝ አመሰግነዋለሁ›› ትላለች።

በውድድሩ ወቅት የነበረው ሞቃታማ የአየር ሁኔታ ለበርካታ አትሌቶች ከባድ ነበር። ነገር ግን አማኔ ብዙም የተቸገረች ሳትመስል ነበር ውድድሯን በስኬት የፈጸመችው። ከዚህ ቀደም የሮጠችባቸው የዱባይ፣ ሙምባይ፣ ቦስተን፣... ማራቶኖች በሞቃት ነበሩ፤ ስለዚህም አማኔ በሞቃት የአየር ሁኔታ መሮጥ ምቾት ሰጥቷታል።‹‹ከቫሌንሲያ በቀር የተወዳደርኩባቸው ማራቶኖች ሞቃት በመሆናቸው ቡዳፔስት ላይ በቀላሉ ላሸንፍ ችያለሁ። ከዝናባማ ይልቅ ሞቃት ስፍራን ለውድድር እመርጣለሁ፤ በእርግጥ በቫሌንሲያ ማራቶን በዝናባማ የአየር ሮጬ የተቀደምኩት በተለየ ምክንያት እንጂ በአየሩ አልነበረም›› ብላለች።

አዲሷ የዓለም ቻምፒዮን ቀጣይ ዕቅዷ መጪው ጊዜ የኦሊምፒክ እንደመሆኑ ‹‹የወደፊቱን የሚያውቀው ፈጣሪ ነው፤ የእኔ ፈንታ መሥራት ነው›› ስትል አስተያየቷን ሰጥታለች።

አምና የቻምፒዮናውን ክብረወሰን በመስበር ያሸነፈችው የዘንድሮው የብር ሜዳሊያ አሸናፊ ጎተይቶም በበኩሏ ‹‹በቡዳፔስት የነበረው ግብግብ ከአትሌቶች ጋር ሳይሆን ከአየር ሁኔታው ጋር ነበር። ፈታኙ ሁኔታም እሱ ነበር፤ ግን ጠንክረን በመሥራታችን ሁኔታውን ተቋቁመን ለድሉ ልንበቃ ችለናል›› ትላለች።

ወጣቷ አትሌትም በተከታታይ ቻምፒዮናዎች ወርቅና የብር ሜዳሊያ ስታስመዘግብ በኢትዮጵያ ማራቶን ታሪክ ብቸኛዋ ሴት አትሌት ነች። ይህንን ተከትሎም የፈጠረባትን ስሜት ‹‹ያሸነፍኩ ያህል ነው የተሰማኝ›› ስትል ትገልጻለች። ‹‹እንኳን በአንድ ዓመት በሁለት ዓመትም ቢካሄድ እንዲህ ዓይነት ውጤት ማግኘት ከባድ ነው። ለእኔ ይህ ትልቅ ድል ነው፤ በሠራሁት መጠንም ጥሩ ሮጫለሁ›› በማለትም ተናግራለች።

ጎተይቶም በኦሪጎኑ ዓለም ቻምፒዮና በድንቅ ብቃት ወርቅ ስታስመዘግብ በወቅቱ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በነበረው ጦርነት ከቤተሰቦቿ ጋር መገናኘት አልቻለችም ነበር። በዚያ የተረበሸ ስሜት ውስጥ ሆና ለስኬት መብቃቷ አስገራሚ ነበር። አሁን ደግሞ ቡዳፔስት ላይ ከደረሰባት ከባድ ኀዘን በቅጡ እንኳን ሳታገግም ነበር የሮጠችው። እነዚህ ከባድ የስሜት መፈራረቆች ግን አትሌቷን ሊበግሯት አልቻሉም። ጎተይቶም ውድድሩን ስትጨርስ እጅግ የተደሰተችውም አንድም በዚሁ ምክንያት ነው። ‹‹ወደ አቋሜ እመለሳለሁ የሚል ሃሳብ አልነበረኝም። በእርግጥ የወንድም ኀዘን ከባድ ነው፤ ያውም ታናሽ ወንድሜን ነው ያጣሁት። ከዚያ በኋላ በቦስተን ማራቶን ሮጬ ከብዶኝ ስለነበር ውጤቴ እንዲህ ይቀጥል ይሆን? በዓለም ቻምፒዮናውስ እንዴት እሆን ይሆን? እያልኩ ሳስብ ነበር። ነገር ግን ስፖርት እንደመሆኑ ጽናት ይፈልጋል፤ ያለፈው አልፏል ውጤቴ ወደኋላ ቢመለስም ወንድሜን ግን ልመልሰው አልችልም። ጠንክሬ በመሥራት የማገኘው ሜዳሊያ ለወንድሜ መታሰቢያ ይሆናል በሚል በጽናት ሮጫለሁ›› ትላለች እንቁዋ አትሌት ከዓለም ቻምፒዮናው በፊት የገጠማትን ስታስታውስ።

‹‹ሁሌም በመንፈስ ጠንካራ ነኝ፣ ከዚህ የበለጠ ውጤት ለማምጣት እጥራለሁ። በዓለም ቻምፒዮና ለሁለት ጊዜ ተሳትፌ ባለ ሜዳሊያ ሆኛለሁ፤ በኦሊምፒክ ደግሞ ተካፍዬ አላውቅም። በመሆኑም እቅዴ ለመጀመሪያ ጊዜ በኦሊምፒክ ተሳታፊ ለመሆንና ጠንክሬ በመሥራት የሜዳሊያ ባለቤት መሆን ነው›› በማለትም ቀጣይ እቅዷን ጠቁማለች።




# ልጆች ለአዲስ ዓመት ምን አቅዳችኋል?

እዮሩስ ተስፋዬ

ሠላም ልጆች እንዴት ናችሁ? ክረምቱ አልቆ ለበጋ ተራውን ሊለቅ ትንሽ ቀናት እንደቀሩት ታውቃላችሁ አይደል? ክረምቱን ቤተሰብ በማገዝ፣ በጨዋታ፣ በንባብ፣ የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመውሰድ፣ የክረምት ትምህርት በመማር፣ ዘመድ በመጠየቅ፣ የጓሮ አትክልቶችን በመንከባከብ፣ የእጅ ሥራዎችን በመሥራት፣ በበጎ ፈቃደኝነት በማገልገል እና መሰል ተግባራትን በመከወን እንዳሳለፋችሁ ምንም ጥርጥር የለኝም።

‹‹መስከረም ሲጠባ፤ አደይ ሲፈነዳ
እንኳን ሰው ዘመዱን፤ ይጠይቃል ባዳ››

ብሎ አዲስ ዓመትን ለመቀበል የአንድ ሳምንት ዕድሜ ብቻ ነው የቀረን። ታዲያ አዲስ ዓመት ሲመጣ ብዙ ሰዎች እቅድ ያወጣሉ። እቅድ ማውጣት ብቻ ሳይሆን እንዴት እንደሚተገብሩት በዝርዝር ጽፈው ያስቀምጣሉ። ‹‹በቃል ያለ ይረሳል፤ በጽሑፍ ያለ ይወረሳል›› እንደሚሉት አባቶቻችን እቅዳቸውን እንዳይዘነጉት ይጽፉታል። ልጆች እናንተስ? አዲስ ዓመትን ለመቀበል ምን ዝግጅት እያደረጋችሁ ነው? እንዴትስ ለማሳለፍ ነው ያቀዳችሁት? ሴቶች ‹‹አበባ አየሽ ወይ?›› ብላችሁ ለመጨፈር፤ ወንዶች ደግሞ ‹‹እንኳን አደረሳችሁ›› ለማለት፣ የእንቁጣጣሽ ሥዕል በመሳል እንዲሁም በአቅራቢያችሁ ለማደል አልተዘጋጃችሁም? ‹‹ተዘጋጅተናል›› የሚል ምላሽ እንደምትሰጡኝ እተማመናለሁ።

ልጆች ዛሬ ስለ እቅድ እንድንነጋገር ወደድን። እቅድ ማውጣት የሚጠቅመው ለምን መሰላችሁ?



የምታከናውኗቸው ነገሮች ቅደም ተከተል እንዲኖራቸው እና ትኩረታችሁም የምትሠሩት ሥራ ላይ ብቻ እንዲሆን ያግዛችኋል። በተጨማሪም ያቀዳችኋቸውን ነገሮች እንዴት መከወን እንደሚቻል እና መቼ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ የተጠና አካሄድ እንዲኖራችሁ ይረዳችኋል። ልጆችዬ እናንተ ተማሪዎች ስለሆናችሁ በትምህርታችሁ ጥሩ ውጤት ልታመጡ የምትችሉበትን መንገድ ማወቅ ይኖርባችኋል አይደል? ስለዚህ እቅድ ማውጣት አለባችሁ። እንዴት እንደሚታቀድ ካላወቃችሁ ደግሞ የወላጆቻችሁን ወይም የመምህሮቻችሁን እርዳታ መጠየቅ ያስፈልጋችኋል። እናም ልጆች ማቀድ በትምህርታችሁ ጎበዝ እንድትሆኑ ከማድረግ ባለፈ ለወደፊት ሕይወታችሁ እንዲሁም ምኞታችሁን ለማሳካት በሚገባ ያግዛችኋል።

ልጆች ከእናንተ ቤተሰብ፣ ሀገር ብዙ እንደሚጠብቅ ታውቃላችሁ አይደል? የነገ ሀገር ተረካቢ ዜጎች መሆናችሁን አውቃችሁ መቼ መጫወት እንዳለባችሁ፤ መቼ ደግሞ ማጥናት እንዳለባችሁ በማቀድ በትምህርታችሁ ውጤታማ እንድትሆኑ ያስችላችኋል። እቅዳችሁ እንዲሳካ ደግሞ ሁልጊዜም እንደምንላችሁ ወላጆቻችሁ ጓደኞቻቹ አሊያም ለቅርብ ቤተሰባችሁ በማማከር እና በመንገር መሆን ይኖርበታል። እንዲሁም እቅዳችሁን በዝርዝር በመጻፍ የዕለት፣ የሳምንት፣ የወር ... እቅዳችሁን ከመጻፍ በዘለለ፤ ምን ያህሉን እንዳሳካችሁ? ለምን እንዳላሳካችሁ? ራሳችሁን በየጊዜው በመፈተሽ እና በማረም ውጤታማ መሆን ትችላላችሁ።

ከዚህ ጋር በተያያዘም ለአዲስ ዓመት አሁንም ጥቂት ቀናቶች እንዳላችሁ በመረዳት፤ የደንብ ልብሶቻችሁን በማዘጋጀት፣ ቦርሳችሁ የሚታጠብም ከሆነ በማጠብ፣ አዲስ የሚገዛላችሁ ከሆነ በጥንቃቄ በመያዝ ለትምህርት የሚያግዟችሁን ቁሳቁሶች ማዘጋጀት ይጠበቅባችኋል።

በትምህርታችሁ ጎበዝ እንድትሆኑም ያለፈውን ዓመት ደብተራችሁን ፈተሽ ፈተሽ በማድረግ ራሳችሁን ማዘጋጀትም ከእናንተ ይጠበቃል። በአዲስ ዓመት የምትማሯቸውን የትምህርት ዓይነቶችም ከታላላቆቻችሁ በመጠየቅ፤ አጋጣሚው እና ሁኔታው ከተመቻቸላችሁ ደግሞ ትምህርታዊ የቴሌግራም ቻናሎችን በመከታተል መዘጋጀት ትችላላችሁ።

አስተውላችሁ ከሆነ ልጆች፤ በብዙ ነገር ጎበዝ የሆኑ ልጆች አሉ። ለምሳሌ በትምህርታቸው ጎበዝ ሆነው ሥዕል መሳል የሚችሉ፣ ጨዋታዎችን ከጓደኞቻቸው ጋር የሚጫወቱ፣ ቤተሰባቸውን የሚያግዙ፣ መጽሐፍትን የሚያነቡ ብዙዎች ናቸው። እንዴት ይህንን ማድረግ ቻሉ? ብላችሁ አልጠየቃችሁም? መልሱ ምን መሰላችሁ? እቅድ አውጥተው በመንቀሳቀሳቸው ነው።

ስለዚህም አሮጌውን 2015 ዓመት እንዴት እንዳሳለፋችሁ በማጤን፤ ምን ዓይነት ስህተቶችን እንደሠራችሁ እና እነዚያን ስህተቶች በአዲሱ ዓመት ላለመድገም ማቀድ ይኖርባችኋል። ሌላው ደግሞ በትምህርት ቤት፣ በሠፈራችሁ እንዲሁም ከቤተሰባችሁ ጋር የተጣላችሁ ትኖራላችሁ። ለመታረቅ አላሰባችሁም? በእርግጠኝነት መልሳችሁ ‹‹አስበናል›› የሚል እንደሆነ አልጠራጠርም። እናም ከሁሉም ሰው ጋር በፍቅር፣ በደስታ እንድትኖሩ እና አዲሱ ዓመት በይቅርታ፣ በፍቅር እና በደስታ እንድታከብሩ የበደላችሁን ‹‹ይቅር›› ማለት፤ እናንተን የበደላችኋቸውን ሰዎች ደግሞ ‹‹ይቅርታ አድርጉልኝ?›› በማለት እርቅ መፍጠር ይኖርባችኋል።

ሌላው ልጆች ከትምህርታችሁ ጎን ለጎን የሚያስደስታችሁን ነገር ለማድረግ አላሰባችሁም? ለምሳሌ የፈጠራ ሥራ የመሥራትም ይሁን ሌላም ፍላጎት ቢኖራችሁ ከትምህርታችሁ ጋር ሳይጋጭባችሁ በእቅዳችሁ መሠረት ማሳካት ትችላላችሁ። ክረምቱን በጨዋታ፣ ቴሌቪዥን በመመልከት በሚገባ ያሳለፋችሁ አላችሁ አይደል? እናም ልጆች ቴሌቪዥን ይሁን ለትምህርታችሁ የማይጠቅማችሁን ነገሮችን በመቀነስ፤ ትምህርታችሁ ላይ በሚገባ ትኩረት አድርጎ መንቀሳቀስን በእቅዳችሁ ውስጥ ብታስገቡ መልካም አይመስላችሁም?

የእናንተ ወላጆች እንዲደሰቱባችሁ፤ ሀገራችንም በእናንተ የምትኮራባችሁ እንድትሆኑ ትምህርታችሁን በሚገባ በመከታተል፣ የቤት ሥራ በመሥራት፣ ያልገባችሁን በመጠየቅ እንዲሁም ከጓደኞቻችሁ ጋር በጋራ በማጥናት ጎበዝ ተማሪዎች ለመሆን እንዳቀዳችሁ ምንም ጥርጥር የለኝም። ታዲያ እቅድ ስለታቀደ ብቻ ማሳካት አይቻልም። ከዚህ ይልቅ ወደ ተግባር በመቀየር ያሰባችሁትን ማሳካት ትችላላችሁ።